# <u>ቃለ - ጉባዔ</u>

- **የስብሰባው አጀንዳዎች/ርዕሰ-ጉዳዮች**፡1. የኢትዮጵያ የቅጂና ተዛማች መብቶች ሕግ ቅኝት፤
  2.የቅጂና ተዛማች መብቶች ማሻሻያ አዋጅ ላይ የቀረበ
  ጥናት፤ እና
  3. የኮፒራይት የጋራ አስተዳደር አመሠራረት እና አሠራር
  በንጽጽር የሚሉናቸው፡፡
- **ፅሁፍ አቅራቢዎች**፡-እንደ አጀንዳው ቅደምተከተል-
  1. አቶ ታምራት ኪዳነማሪያም (የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት እንዲሁም የሕግ አማካሪና ጠበቃ)
  2. አቶ ወሰን ሙሉ (በአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በኮፒራይት ዳይሬክቶሬት የቅጂ መብት ሕጋዊ ተፈፃሚነት ቡድን መሪ)
  3. ወ/ሪት ሠብለ ገብረጊዮርጊስ (የሕግ አማካሪና ጠበቃ እንዲሁም በዘርፉ ልምድ ያላቸው ባለሙያ)
- **አወያይ**፡-አቶ ደረጀ ወርቁ /የሕግ አማካሪና ጠበቃ/
- **የስብሰባው ቦታ**፡- የአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት
- **በስብሰባው ላይ የተገኙ**፡- የማኅበሩ አባላት፣ የሕግአማካሪዎችና ጠበቆች፣ የመንግሥት ሠራተኞች፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተወካዮች፣የአርት ሙያ ማኅበራት ተወካዮችና ሌሎችም
- **የስብሰባው ቀን**፡- ታኅሳስ 15 ቀን 2009 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3፡00 እስከ ከቀኑ 9፡30 ሠዓት

## <u>አቶ ደረጀ ወርቁ - አወያይ (የሕግ አማካሪና ጠበቃ)</u>

አወያዩ የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ካስተላለፉ በኂላ በእለቱ የሚቀርቡ 3 ጽሁፎች በተለያዩ ባለሙያዎች አማካኝነት መሆኑን ጠቅሰው የመጀመሪያው በማህበሩ ፕሬዝዳንት በአቶ ታምራት ኪዳነማሪያም የሚቀርብ ሲሆን በቀጣይም በአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በኮፒራይት ዳይሬክቶሬት የቅጂ መብት ሕጋዊ ተፈፃሚነት ቡድን መሪ በሆኑት በአቶ ወሰን ሙሉ ማሻሻያዎችን የሚመለከት ሲሆን በመጨረሻም የሕግ አማካሪና ጠበቃ በሆኑት በወ/ሪት ሠብለ ገብረጊዮርጊስ አማካኝነት የሚቀርብ ፅሁፍ ይኖረናል ብለዋል፡፡ ባለሙያዎቹ የሚያቀርቡልን ፅሁፎችም በዋናነት የቅጂና አጎራባች መብቶች ላይ እንደሚሆን ጠቁመው ወደ ፅሁፍ ማቅረቡ ከመግባታችን በፊት የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዝዳንት የሆኑትና የመጀመሪያውን ፅሁፍ የሚያቀርቡልን አቶ ታምራት ኪዳነማሪያም አጭር መልዕክት እንዲያስተላልፉ እድል ሰጥተዋል፡፡

## አቶ ታምራት ኪዳነማርያም - ፅሁፍ አቅራቢ፣ የማኅበሩ ፕሬዝዳንት እንዲሁም የሕግ አማካሪና ጠበቃ

አቶ ታምራት ኪዳነማርያም የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክታቸውን ካስተላለፉ በኋላ ማኅበሩ ከአዕምሯዊ ንብረት ፅ/ቤት ጋር በመተባበር በዕለቱ የተሰናዳው ትምህርታዊ ውይይት የኢትዮጵያ የቅጂና ተዛማች መብቶች ሕግ፤ የኮፒራይት የጋራ አስተዳደር ማኅበራት አመሠራረት እና አሠራር በንጽጽር፤ እና የቅጂና ተዛማች መብቶች ማሻሻያ አዋጅ ላይ የቀረበ ጥናትን በሚመለከት ሲሆን ጥናታዊ ጽሑፎቹም እርሳቸውን ጨምሮ በሌሎች ባለሙያዎች ጭምር የሚቀርብ መሆኑን ጠቅሰው ዐውደጥናቱ እንዲዘጋጅ ስፖንሰር በማድረግ ወይም ወጪዎችን በመሸፈን ብቻ ሳይሆን ጥናታዊ ፅሁፍም በማቅረብ ጭምር አስተዋጽዖ ያደረጉ በመሆናቸው ለአእምሯዊ ንብረት ፅ/ቤት የላቀ ምስጋና አለኝ ብለዋል፡፡

የኢትዮጵ የሕግ ባለሙያዎች ማሕበር የአእምሯዊ ንብረት ኮሚቴ ያቋቋመ ሲሆን ሰብሳቢውም አቶ ጌታቸው መንግሥቴ መሆናቸውን ጠቅሰው እርሳቸው ከኮሚቴው ጋር በመሆን የተለያዩ ሥራዎችን በመስራት ላይ የሚገኙ እንደሆነ ገልፀው በዚህ ዓመት ግንቦት ወር ላይም በንግድ ምልክት (trade mark) ላይ ዐውደጥናት ለማዘጋጀት እቅድ ስለመያዙ አውስተው በእለቱ የመጡ ታዳሚ ተሳታፊዎችን አመስግነዋል፡፡

## አቶ ደረጄ ወርቁ - አወያይ (የሕግ አማካሪና ጠበቃ)

አቶ ታምራት ኪዳነማሪያም ካስተላለፉት አጭር መልዕክት በመቀጠል አወያዩ መድረኩን የተረከቡ ሲሆን የቅጂ መብት ምንነት እና ተዛማጅ መብቶች ላይ የማኅበሩፕሬዝዳንት ፅሁፋቸውን የሚያቀርቡ ሲሆን በአእምሯዊ ንብረት መብት ዙሪያ specialize ያደረጉ፣ የአእምሯዊ ንብረት ሕግ ረቂቅ በሚዘጋጅበት ወቅት ተሳታፊ የነበሩ እንዲሁም በዘርፉ ሲያስተምሩ የነበሩ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ ቀጣይ ፅሁፍ አቅራቢ አቶ ሙሉ ወሰን በበኩላቸው በአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ውስጥ የሚሰሩ ባለሙያ በማሻሻያ አዋጁ ላይ ፅሁፍ የሚያቀርቡ ሲሆን በፅ/ቤቱ ከመስራታቸው ባሻገር ሕጉ በሚሻሻልበት ጊዜ ግብዓት በመስተት ተሳትፈዋል ብለዋል፡፡ በመጨረሻም ወ/ሪት ሠብለ ገብረጊዮርጊስ በአእምሯዊ ንብረት መብቶች በንጽጽር ጽሁፍ የሚያቀርቡልን ሲሆን በዘርፉም የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርታቸውን በመማር specialize ያደረጉ መሆናቸውን ከገለፁ በኋላ በቀጥታ አቶ ታምራት ፅሁፋቸውን እንዲያቀርቡ ጠይቀዋል፡፡

## አቶ ታምራት ኪዳነማርያም - ፅሁፍ አቅራቢ፣ የማኅበሩ ፕሬዝዳንት እንዲሁም የሕግ አማካሪና ጠበቃ

መድረኩ ስለተሰጣቸው አመስግነው የኢትዮጵያ የቅጂና ተዛማጅ መብቶች ሕግ ቅኝት በሚል ርዕስ ያዘጋጁትን ፅሁፍ የሚያቀርቡ ሲሆን በጊዜ መጣበብ ምክንት ለተሳታፊዎች የተሰራጨው ጥራዝ ፅሁፍ የመጀመሪያ ረቂቅ (first draft) በመሆኑ የediting ችግር ሊኖርበት የሚችል መሆኑን ጠቁመው በቀጥታ ወደ ገለፃው የገቡ ሲሆን የአዕምሯዊ ንብረት መብቶች የምንላቸው በልዩ ልዩ የአዕምሮ ውጤቶች (ንብረቶች) ላይ የሚያርፉ፣ በህግ የተሰጡ እና ለባለቤቱ የኢኮኖሚ ጥቅም የሚያስገኙ መብቶችናቸው በማለት እነዚህ መብቶቹን ከመደበኛዎቹ ግዑዛዊ ካልሆኑ ንብረቶችለምሣሌ አክሲዮን፣ ቼክ፤ የሐዋላ ወረቀት፣ የገንዘብ ኖቶች፣ ቦንድ፣ ድርሻ ወዘተ. ጋር ተመሳሳይ እንደሆኑ በማስረዳት መብቶቹን ለመገልገል የተወሰኑ ቅድመሁኔታዎች መሟላት እንዳለባቸው ጠቁመዋል። የአእምሯዊ ንብረቶች ወዲያው በቀጥታ ጥቅም ላይ የሚውሉ አይደሉም ብለዋል።

የአዕምሯዊ ንብረቶች በዋናነት ለሶስት የሚከፈሉ ሲሆን እነኝህም፦

1. የቅጂና ተዛማጅ መብቶች፣
2. የኢንዱስትሪያዊ ንብረት መብቶች እና
3. የልማዳዊ/ባሕላዊ እውቀት/የሀገር በቀል እውቀት (traditional knowledge and folklore) መብት ናቸው።

የቅጂና ተዛማጅ መብቶችን በስፋት የምንመለከት ሲሆን የኢንደስትሪያዊ ንብረት መብቶች በበኩላቸው ቴክኒካዊ ችግርን ለሚፈቱ ፈጠራዎችና አነስተኛ ፈጠራዎች የሚሰጡ የፓተንትና የግልጋሎት ሞዴል የምሥክር ወረቀት መብቶችን፣ የምርት ቅርጽንና መልክን ለሚመለከቱ ፈጠራዎች የሚሰጠውን የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ የምሥክር ወረቀት መብትን፣የንግድ ምሥጢርን የመያዝ መብትን፣ ከማይገባ ውድድርና ተገቢ ካልሆነ የንግድ አሠራር የመጠበቅ መብትን፣ የንግድ ምልክት መብትን፣ የንግድ ስምና መልካም ዝናን የመጠበቅ መብትን ወዘተ የሚካትቱ ናቸው በማለት ከዘረዘሩ በኋላየልማዳዊ እውቀት አሁን አሁን እውቅና እየተሰጠው የመጣ መብት መሆኑንንም አስቀምጠዋል።

የቅጂና ተዛማጅ መብቶች በሁለት የሚከፈሉ መሆናቸውን የቅጂ መብት (copyrights)ለስነጽሑፍ እና ለአርት ሥራዎች ጥበቃ የሚሰጡ በተለይም የማባዛት የማከፋፈል መብቶች ወዘተ መሆናቸውን፤ የተዛማጅ መብቶች (neighboring rights) ደግሞ ለከዋኞች፣ ለድምጽ ሪከርዲንግ ባለቤቶች እና ለብሮድካስተሮች (ለሬዲዮና ቴሌቪዥን ፕሮግራሞች) የሚሰጡ መብቶች መሆናቸውን በመከፋፈል አስረድተዋል፡፡

በቅጂ ሕጉ መሠረት ጥበቃ የሚደረገው ለመልዕክቱ ወይም ለሃሳቡ ሳይሆን ሃሳቡ የተገለፀበትን አኳኋን (expression of ideas) ነው፡፡ የቅጂና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 410/1996 በአንቀጽ 2 (30) ስር ሥራዎች (works) በሚል የተቀመጡ ነገሮች ያሉ ሲሆን ድንጋጌውም እንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡

*<u>አንቀፅ 2 - ትርጓሜ</u>*

.....

*(30) ‹‹ሥራ›› ማለት የሥነ-ፅሁፍ፣ ኪነጥበብ እና ሳይንሳዊ መስኮች ውጤት ሆኖ በተለይ የሚከተሉትን ይጨምራል፣*

*ሀ. መፅሐፍ፣ ቡክሌት፣ በመፅሄት ወይም በጋዜጣ ላይ የሚገኝ መጣጥፍ፣ የኮምፒውተር ፕሮግራም፣*

*ለ. ንግግር፣ ሌክቸር፣ ለአንድ ለተወሰነ ክፍል የሚደረግ መልዕክት አዘል ንግግር፣ የሓይማኖት ስብከት፣ እና ሌላ በቃል የቀረበ ሥራ፣*

*ሐ. ድራማ፣ ድራማዊ የሙዚቃ ሥራ፣ በእንቅስቃሴ ብቻ የሚቀርብ ድራማ (ፓንቶማይምስ) የመድረክ ውዝዋዜ እና ሌላ ለመድረክ ተብሎ የሚሰራ ሥራ፣*

*መ. የሙዚቃ ሥራ፣*

*ሠ. የኦዲዮቪዧል ሥራ፣*

*ረ. የኪነሕንፃ ሥራ፣*

*ሰ. የሥዕል፣ የቅብ፣ የሀውልት፣ የቅርፃ ቅርፅ፣ የህትመት፣ የፊደል ቅርፅ፣ ጥልፍና ሌላ የሥነጥበብ ስራ፣*

*ሸ. የፎቶግራፍ ሥራ፣*

*ቀ. ስዕላዊ መግለጫ፣ ካርታ፣ ፕላን፣ ንድፍ እና ባለ ሶስት ገጻታ ከጂኦግራፊ፣ ቶፖግራፊ፣ ኪነሕንፃ ወይም ሳይንስ ጋር የተያያዘ ሥራ፣*

በመሆኑም በአዋጁ ሥራ ተብለው ለተመደቡ የፈጠራ ዓይነቶች በሙሉ በመሆኑ በሕጋችን የኦዲዮቪዡዋል ሥራዎች ለመደበኛዎቹ የስነጽሑፍና የኪነጥበብ ሥራዎች የሚደረግላቸው የቅጂ መብት ጥበቃ ይደረግላቸዋል ማለት ነው ብለዋል፡፡

በተዛማጅ መብትነት ጥበቃ የሚደረግላቸው ፈጠራዎችክወና፣ ብሮድካስት እና የድምፅ ሪከርዲንግ መሆናቸውንና በአዋጁ ከአንቀፅ 26 እስከ 32 ድረስ ባለው የተሸፈኑ መሆኑን ጠቅሰው ለምሳሌ ያህል ፍቅር እስከመቃብር የተሰኘውን ልበወለድ በወጋየሁ ንጋቱ ሲተረክ ይሄ እንደ ክወና (performance) የሚታይ እና ጥበቃ የሚደረገውም በተዛማጅ መብቶች እንጂ በቅጂ አይደለም ብለዋል፡፡ የድምፅ ሪከርዲንግ ሥራዎችለምሣሌ ካሴቶች፣ በድምፅ ብቻ የተቀረጹ ሲዲዎች በተዛማጅ መብትነት ጥበቃ ሲደረግላቸው የኦዲዮቪዡዋል ሥራዎች (በአንቀፅ 2 (30) (ሠ)) ግን የቅጂ መብት ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ እነዚህንሁለት የሥራ ዓይነቶች መለያየት ለምን አስፈለገ የሚል ጥያቄ ያነሱ ሲሆን ይህን በሚመለከት አቶ ጌታቸው መንግሥቴ እንደሚሉት የምስል ቀረፃ ከድምፅ ቀረፃ በላቀ ሁኔታ የበለጠ ጥበብ የሚጠይቅና አድካሚ በመሆኑ ምክንያት ሰፋ ያለና የተሻለ ጥበቃ ተደርጎለታል ብለዋል፡፡ የፊልም ሥራዎች ከተዋናይ አክተሮች መረጣ ጀምሮ ብዙ ሙያዊ ሥራ እና የዳይሬክቲንግ ፈጠራ የሚጠይቅ ሲሆን የድምጽ ሪከርዲንግ ሥራዎችም የሚጠይቁት ጥበብ ቢኖርም በተነጻጻሪነት ሲታዩ ከፈጠራነት ይልቅ ወደ ንግድነትና ኢንቨስትመንትነት ያመዝናሉ፤ በመሆኑም አዋጁ አነስ ያለ ጥበቃ ሰጥቷቸዋል ብለዋል፡፡

የቅጂ መብት ጥበቃ ለማግነት መሟላት ያለባቸው ሁለት መሠረታዊ ነገሮች ያሉ ሲሆን እነዚህም፡-

1. ወጥነት እና
2. መቀረፅ እና በግዙፍነት መገኘት ናቸው ብለዋል፡፡

ሥራው ወጥ (ኦርጅናል) መሆን አለበት ሲል ከሥራ አመንጪው የፈለቀ ወይም ከሌላ ሥራ ያልተቀዳ መሆን አለበት ለማለት እንደሆነ፤ ይህ ማለት ግን ሥራው የግድ አዲስ መሆን አለበት ማለት እንዳልሆነ በአፅዕንዎት አስረድተዋል፡፡ ይህንኑ በምሳሌ ሲያስረዱ የእግር ኳስ ትዕይንትን የሚዘግቡ ጋዜጠኞች ተመሳሳይ ነገር ሊናገሩ ይችላሉ ብለዋል፡፡ በሌላ ምሳሌ የጎንደር የአጼ ፋሲል ቤተመንግሥትን ከበስተምሥራቅ አቅጣጫ በተለያዩ ባለሙያዎች የተነሱ ፎቶግራፎች ቢመሣሰሉ ሊያስገርም የማይገባ ከመሆኑም በላይ ሁሉም ጥበቃ ይደረግላቸዋልብለዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር ሥራዎቹ ወጥ (ያልተኮረጁ) ይሁኑ እንጂ ጥራታቸውን የጠበቁ አለመሆናቸው ጥበቃ ከማግኘት አያግዳቸውም ሲሉ አክለዋል፡፡ስለዚህ ስራው ጥራት ቢያንሰውም ታስቦ የተሰራ ወይም የሀሣብ

ውጤት መሆን አለበት። ከፓተንት ጋር በተነፃፃሪነት ሲታይ ፓተንት የሚሰጠው ለችግር ፈቺ አዲስ ፈጠራ እና በመስኩ የሰለጠኑ ሙያተኛ በቀላሉ ሊያገኘው የማይችለው ሲሆን ብቻ እንደሆነ ጠቅሰው የኮፒራይት መብት ጥበቃ ቅድመሁኔታ ግን ከዚህ በእጅጉ ያነሰ እንደሆነ አስረድተዋል።

በቅጂና ተዛማጅ መብቶች አዋ.ቁ 410/1996 ዓ.ም አንቀጽ 6 (1) ላይ የሥራዎቹ ዓላማ ምንም ይሁን ምንም ግምት ውስጥ ሳይገባ ሥራዎቹ ጥበቃ ያገኛሉ የሚል መሆኑን ጠቅሰው ሥራው ለመልካም ፀባይ ተጻጻሪ፣ ሞራል የሚነካ ወይም ለፖሊሲ ተቃራኒ ቢሆንም ጥበቃ የሚሰጥ መሆኑን ጠቅሰው በፓተንት ግን ይሄ እንደማይቻል አስረድተዋል። የፍትኃብሄር ሕጉ በአንቀፅ 1716 (1) እንደተመለከተው ውል በተዋዋይ ወገኖች ላይ ከመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆነ ግዴታን የሚጥል እንደሆነ ውሉ ፈራሽ እንደሆነ እንዲሁም አንቀፅ 1677 ደግሞ ግዴታዎች ከውል የተገኙ ባይሆኑም የዚህ አንቀፅ ተፈፃሚነትን የማይከለክል በመሆኑ በኮፒራይት አዋጁ ጥበቃ የሚሰጠው ከሞራል ተቃራኒ የሆነ ሥራ ከፍትሓብሔር ሕጉ ጋር እንዴት ሊጣጣም ይችላል የሚል ጥያቄ ያነሱ ሲሆን የአዋጁ ዓላማ ሳንሱር ለማስወገድ መሆኑን ነገርግን የፕሬስ ሕጉ መተላለፍ ግን አግባብነት ባለው አንቀፅ ሊያስጠይቅ እንደሚችል አስገንዝበዋል።ሥራው የፕሬስ ሕጎች የሚጥስ እና የወጣቶችን መልካም ጸባይና አስተዳደግ የሚያውክ ሆኖ ቢገኝ እና በሌላ በኩል ግን ሥራው በሕገወጥ መንገድ ቢባዛ ባለመብቱ ሰው ያለፈቃድ ያባዙትን ሰዎች በሕግ ሊጠይቅ ይችላል? ካሳስ ሊቀበል ይችላል? የሚሉ ጥያቄዎችን አንስተዋል።ሥራውን በመሸጥ ሊያገኝ ይችል የነበረው ገቢ በራሱ መልካም ጸባይን እና ሕግን የሚጻረር ስለሆነ በአከፋፋዮቹ ላይ ይህንን ሕገወጥ ጥቅም የመተካት ሕጋዊ ግዴታ ሊፈጠር አይችልም። ነገርግን በሕገወጥ ያባዙትና ያከፋፈሉት ሰዎች ነጻ ሊሆኑ የሚችሉት የፈጠራ ባለቤቱን ሕገወጥ ጥቅምን ከመተካት ነው እንጂ በወንጀል መጠየቃቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች ሕጋዊ ጥቅሙን ለመካስ የሚገደዱ መሆኑን በማጣቀሻነትም የቹቹኒዮዊች አቋምን ገልፀዋል። ለምሣሌ ሥራውን ያለባለቤቱ ፈቃድ በማባዛታቸውና በማሰራጨታቸው የሞራል ካሣ መክፈል አለባቸው በማለት መከራከር እንደሚቻል አብራርተዋል።

ለኮፒራይት ጥበቃ ሌላኛው ቅድመሁኔታ በግዙፍነት ተቀርፆ መቀመጥ መሆኑን አስታውሰው በፍትሓብሔር ሕጉ መቅረፅ እንደቅድመሁኔታ ያልተቀመጠ መሆኑንና በአዋጁ እንዲገባ የተደረገ አዲስ ቅድመሁኔታ መሆኑን ጠቅሰው ይህም ያስፈለገበት ምክንያት የተለያዩ ትውፊቶችና የቃል ታሪኮች ለትውልድ እንዲተላለፉ ያግዛል የሚል እንደሆነም ጠቁመዋል። ሥራው በጽሑፍ፣ በድምጽ፣ በምስል፣ በዲጂታል ወይም በማናቸውም አሁን ባሉ እና ወደፊት በሚመጡ የቴክኖሎጂ ዘዴዎች ሊቀረጽ የሚገባው መሆኑን ጠቅሰው አንድ አንድ ሥራዎች በባህሪያቸው ካልተቀረፁ

ሊፈጠሩም አይችሉም በማለት በምሳሌ ያስደገፏቸው ሲሆን እነዚህም ስዕል፣ ቅርጻቅርጽ፣ ፊልም፣ የድምፅ ሪከርዲንግ ወዘተ ብለዋል፡፡

ሕጉ ጥበቃ የከለከላቸው ሥራዎች መኖራቸውን በመጠቆም ሕግ ነክ ሰነዶች፣ ፍርዶች፣ የአሠራር ዘዴ፣ የአሠራር ሂደት፣ ሲስተም፣ ሀሳብ፣ ቀመር ወዘተ ሲሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 5 (ሀ) እና (ለ) ተመላክተዋልብለዋል፡፡ ለደራሲ ጥበቃ የሚደረገው ሃሳቡን ሳይሆን የሃሳቡን አገላለፅ (expression of ideas)እንደሆነ አስቀምጠዋል፡፡

የአዕምሯዊ ንብረት ሕግን ከሌሎች ፍትሐብሔራዊ ሕጎች ጋር ስናነጻጽረው አንዱ ልዩ የሚያደርገው ጸባይ ተፈጻሚነቱ በግዛት ድንበር የተገደበ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ታምራት በአዋጁ አንቀጽ 3 (1) ከ(ሀ) እስከ (መ) ላይ እንደተቀመጠው የሕግ ጥበቃ ተፈጻሚ የሚሆነው አንድም ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ ወይም ቋሚ መኖሪያው ኢትዮጵያ ውስጥ በሆነ የሥራ አመንጪ ሥራ ላይ፣ ወይም የሥራ አመንጪው ዜግነት ወይም መኖሪያ ኢትዮጵያ ባይሆንም ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ወይም ውጪ ሀገር በታተመ በ30 ቀናት ውስጥ በኢትዮጵያ በታተመ ሥራ ላይ፣ የፕሮዲውሰሩ ዋና መሥሪያ ቤት ወይም ቋሚ መኖሪያ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደሆነ፣ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ በቆመ ሕንጻ ወይም ስትራክቸር ውስጥ በተካተተ የኪነ ጥበብ ሥራ ላይ እንደሆነ ዘርዝረዋል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ባልሆነ የውጪ ሀገር ዜጋ የተፈጠረውን ሥራ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሳተመው ወይም ሕንጻ ውስጥ ያካተተው እራሱ የሥራ አመንጪው ሳይሆን ሌላ ሰው ቢሆን የውጪው ዜጋ ጥበቃ እንደማያገኝ አስረድተዋል፡፡ ከክወና ጋር በተያያዘ ፅሁፍ አቅራቢው አቶ ታምራት በምሳሌነት ያነሱት ቢዮንሴ በሚሊኒዬም አዳራሽ ውስጥ ፐርፎርም ያደረገችው ወይም የከወነችው ጥበቃ የሚቸረው ሲሆን በሌላ ሀገር የሰራችው ፐርፎርማንስ ግን በእኛ ሀገር ሕግ ጥበቃ እንደሌለው አስረድተዋል፡፡ ይሄ ማለት ግን የቢዮንሴን የውጭ ሥራዎች በማምጣት የራሳችን ማድረግ የማንችል መሆኑን ጠቅሰው ለዚህ ደግሞ ወጥነት የሚለው ቅድመሁኔታ መሟላትን የሚጠይቅ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

የቅጂና የተዛማጅ መብት ዓይነቶችንና ወሰናቸውን በአዋጁ የተቀመጠ ሲሆን መብቶቹ የኢኮኖሚ እና የሞራል መብት ተብለው ለ2 ዋና ዋና ምድቦች የሚከፈሉ መሆናቸውን አክለዋል፡፡ መብቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. *የማባዛት-* በፎቶኮፒ፣ በዲጂታል መሣሪያ፣ በካሜራ፣ በኢሜል፣ በብሉቱዝ፣ ወዘተ እንዲሁም አንድ ሐውልትን በማየት በእጅ መሳልን ጨምሮ የሚያካትት መሆኑን በመግለፅ

ማባዛት ሰፊ ትርጉም ያለው መሆኑን እንዲሁም ዋሳኝ የሚባለውን የሥራ ክፍሉን ከወሰድን እንዳባዛን ነው የሚቆጠረው ካሉ በኋላ መጥቀስ ወይም ሳይት ማድረግ ሪፐርዲውስ ከማድረግ ጋር ያለው ንፅፅር አከራካሪ ሲሆን substantial similarity test ዋሳኝ መለኪያ እንደሆነ የጠቀሱት አቶ ታምራት ይሄ መለኪያ አንዱን ካነበብን ወይም ከተመለከትን ሌላኛውን ማንበብ ወይም መመልከት አያስፈልግም የሚባል እንደሆነ ጠቅሰው አብራርተዋል፡፡

2. *የመተርጎም፡-*አንድን ሥራ ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ መመለስን የሚያመለክት እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡ የምልክት ቋንቋ በመጠቀም የሚገለፁ ነገሮች ትርጉም ወይንስ ማባዛት ናቸው የሚለው አከራካሪ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ ድርሰት ወደ ቲያትር መቀየርስ ማመሳሰል ወይስ ማባዛት የሚለውንም እንዲሁ አንስተዋል፡፡
3. *የማመሳሰል (ማቀናበር/ወደሌላመቀየር)፡-* ማለት በስድ ንባብ መልክ የተቀመጠውን ወደ ግጥም መቀየር፣ በልብ ወለድ ትረካ መልካ የተጻፈውን ወደ ቲያትር መቀየር እንደሆነ በምሳሌ አስረድተዋል፡፡ ለምሣሌ ኮሜዲያኖች ዘፈኖችን ዘና በሚያደርግ ሁኔታ ሲያገጣጥሟቸው ወይም አንዳንዴም አዝናኝ አድርገው ሲያቀርቧቸው የሚስተዋል መሆኑን ጠቅሰው ይህ የአንድን ሰው ሥራ እንደ መቀየር ወይም ማቀናበር ተቆጥሮባቸው ከሥራ አመንጪው ፈቃድ ማግኘትት የሚጠበቅ መሆን አለመሆኑን በመጠየቅ 3 ዓይነት ሁኔታዎችን ማለትም parody- ሥራን ወደ አሥቂኝ መቀየር፣ pastiche- ቀነጫጭቦ ኮሜዲ መስራት፣ እንዲሁም caricature- ወደ ካርቱን ምስሎች መቀየር ያስቀመጡ ሲሆን በፍ/ሕ/ቁ 1654 (1) (2) ና (3) ላይ የማቀናበር መብት ያለው የሥራ አመንጪው ብቻ መሆኑን ካስቀመጠ በኋላ እነኝህ 3 ነገሮች ግን እንደማቀናበር እንደማይቆጠሩ ይደነግጋል ብለዋል፡፡ እንደማመሳሰልም እንደማቆጠሩ ጠቅሰው እነዚህ ሶስቱንም በተመለከተ ደራሲውን ማስፈቀድ ያስፈልጋል ወይስ አያስፈልግም የሚል ጥያቄ ካነሱ በኋላ የውጭ ሀገር ልምድ በማንሳት ደራሲውን ወይም የሥራ አመንጪውን ማስፈቀድ ግዴታ እንዳልሆነ ገልፀው የፍ/ብሔር ሕጉ የሥራ አመንጪው ፈቃድ አያስፈልግም የሚል ሲሆን አዋጁ ይህን ጉዳይ በዝምታ አልፎታል ብለዋል፡፡ አዋጁ ምንም ሳይል በማለፉ ባልተሻረው የፍትሐብሔር ሕግ ላይ በተቀመጠው መሠረት እንደማቀናበር አለመቆጠራቸው ይቀጥላል ማለት ነው ብለዋል፡፡
4. *ለህዝብማሳየት፡-* ስዕል የሆነ እንደሆነ ለህዝብ በኤግዚቢሺን በጋለሪ መልክ ማሳየትን እንደምሳሌ ጠቅሰዋል፡፡

5. *መከወን፡-*ስራው እንዲከወን የመፍቀድና የመከልከል መብትም ያለ ሲሆን ይህ መጫወትን፣ ማነብነብን፣ በድርጊት ማሣየትን፣ ለህዝብ በቀጥታ ወይም በቴክኖሎጂ አማካኝነት ማቅረብን ያካትታል፡፡ ስለዚህ ፊልምን በሚመለከት በሲነማ ቤት ማሳየትን ይመለከታል፡፡ የድምጽ ሪከርዲንግ፣ የክወና እንዲሁም የብሮድካስቲንግ *ሥራዎችን* በሚመለከት ለባለቤቶቹ ይህንን የመፍቀድ እና የመከልከል መብት አልተሰጣቸውም፡፡

ከላይ ከተብራሩት የመብት ዓይነቶች በተጨማሪ *ማከፋፈል (በሽያጭ/ኪራይ)*፣ *ከውጪ ወደ ሃገር ማስገባት መሸጥ*፣ *መቀረጽ*፣ *በሬድዮ ቲቪ ማሰራጨት* (ብሮድካስት ማድረግ)፣ እና *ሥራን በሌላ መንገድ ማሰራጨት* (ለምሣሌ በድረገጽ ማሠራጨት) እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡

አንድ ዲጄ (የሙዚቃ አጫዋች) በምሽት ክበብ ውስጥ ለመከወን ማስፈቀድ የማይጠበቅበት ሲሆን አንድ የብሮድካስት ተቋም አንድ ታትሞ የወጣን ፊልም ለማሳየት ፈቃድ ማግኘት እንዳለበት ጠቁመው ያለፕሮዲውሰር ፈቃድ አንድን ፊልም የብሮድካስት ድርጅት ዌብሳይት ላይ ማስቀመጥ አይችልም በማለት በአፅንዖት ገልፀዋል፡፡

በአጠቃላይ አዋጁ ያስተዋወቀው አዲስ ነገር የመብቶች ተፈፃሚነት ላይ ሰፊ ነገር አስቀምጧል ያሉት ፅሁፍ አቅራቢውፍ/ቤቶች እንዳይባዛ ማገድና ሌሎች እርምጃዎችን እንዲወስዱ የሚያስችል ማዕቀፍን አካቷል ብለዋል፡፡መብቶችን በሕግ ኃይል ማስፈጸም የሚያስፈልገው ሲጣሱ እንደሆነና የመብት ጥሰት የምንለው በዋናነት ለቅጂና ተዛማጅ የሥራ አመንጪ ወይም ባለቤት በሕግ የተሰጠውን መብት ያለባለመብቱ ፈቃድ ሥራ ላይ ማዋል እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

የቅጂ መብት ጥሰት ተጠቂዎች መብት ለማስጠበቅ ሲል ተጎጂው ከካሳ ይልቅ መብት ጣሹ ያገኘውን ትርፍ ለመጠየቅ ከፈለገ በህግ ሥርዓታችን ውስን ከሆኑ ጉዳዮች በስተቀር በተለይ ከጉዳት ጋር በተያያዘ ፈጽሞ ተፈጻሚነት የሌለውን የተከሳሽ ሂሣብ ተመርምሮ ያተረፈው ይከፈለኝ ብሎ መጠየቅ የሚቻልበትን ጽንሰ ሀሳብ (account for profits) ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲያካትት ሆኖዋል ያሉት አቶ ታምራት የፍ/ብሔር ሕጉ ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ ከመደንገግ በቀር ስለ አትርፎ መካስ አያወራም ብለዋል፡፡ በአዋጁ መሠረት ግን መብት ጣሹ ያገኘውን ብልፅግና ለተጎጂው ይሰጣል፤ በትክክል የጉዳጥ መጠኑ ካልታወቀ ፍ/ቤቱ በርትዕ ይወስናል ካሉ በኋላ የሞራል ካሣ ወለሉ ብር 100,000 እንዲሆን ተደርጓል በማለት በፍ/ብሔር ሕጉጋር ልዩነት እንዳለው አስቀምጠዋል*(በፍትሐብሔር ሕጉ ስለ ሞራል ካሣ መጠን በቁ.2116 (3) ተደነገገውን የብር 1000 (አንድ ሺህ) ጣሪያ)*፡፡ከገንዘብ ካሳ በተጨማሪ ተከሣሹ የመብትጥሰቱን አድራጎት እንዲያቆም ቋሚ

ክልከላ (injunction) ሊፈረድበት እንደሚችል በፍ/ሕ/ቁ 2121 ላይ መደንገጉን ገልፀው ነገርግን ይህ የመፍትሄ እርምጃ የሚታዘዘው ምንም እንኳ ግንድና ፍርድ የሚወድቅበት ባይታወቅም ድርጊቱ የተፈጸመ እንደሆነ በገንዘብ የመካስ እድሉ የጠበበ ሲሆንና የመፈጸሙም ዕድል የሰፋ ከሆነበማለት ገለፃቸውን አጠናቀዋል፡፡

## <u>አቶ ደረጄ ወርቁ - አወያይ (የሕግ አማካሪና ጠበቃ)</u>

ፅሁፍ አቅራቢውን አቶ ታምራት ኪዳነማርያምን እጅግ ካመሰገኑ በኋላ የቀረበው ጽሁፍ በጣም ጥልቅ መሆኑን በሰንጠረዥ መልክ የቀረበው እጅግ ጠቃሚና የመብቶቹን ዓይነትና ወሰን ለመለየት የሚያስችል መሆኑን ጠቅሰው ቀጥሎ የሚቀርበው ፅሁፍም ተወራራሽ መሆኑን ገልፀው በቀጥታ ወደሚቀጥለው ፅሁፍ አቅራቢ አቶ ወሰን ሙሉ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ፅ/ቤት ውስጥ የሚሰሩ ባለሙያ ሲሆን በፅሁፋቸውም ላይ ስለ አዋጁ ማሻሻያዎች ላይ በማተኮር ገለፃ የሚያደርጉ መሆኑን ጠቅሰው ወደ መድረኩን ለእርሳቸው አስረክበዋል፡፡

## <u>አቶ ወሰን ሙሉ -በአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በኮፒራይት ዳይሬክቶሬት</u><br><u>የቅጂ መብት ሕጋዊ ተፈፃሚነት ቡድን መሪ</u>

የፅሁፋቸው አርዕስት የቅጂና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 872/2007 ዋና ዋና ጉዳዮች መሆኑን ጠቅሰው የመጀመሪያው ፅሁፉ አቅራቢ አቶ ታምራት አብዛኛውን የአዋጁ ክፍል ስለገለፁ እርሳቸው ደግሞ በማሻሻያዎቹ ላይ የተደረጉ ለውጦች ላይ ተመርኩዘው ጽሁፋቸውን የሚያቀርቡ መሆኑን ጠቅሰው በቀጥታ ወደ ገለጻው የገቡ ሲሆን በየወቅቱ እያደገ የመጣውን የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ እንቅስቃሴ የሚመጥን የህግ ስርዓት ለመዘርጋት እናባለመብቶችን በተደራጀና በተጠናከረ አግባብ መብቶቻቸውን ማስተዳደር የሚችሉበትን ሁኔታ ለመፍጠር እንዲቻል በተሻሻለው አዋጅ የተካተቱ ጉዳዮች መኖራቸውን ከገለጹ በኋላ እነዚህ አዳዲስ መሻሻያዎች የዕደ ጥበብ ስራዎችን፣ ስለ ሮያሊቲ፣ ስለ ጋራ አስተዳደር ማህበር፣ ስለ ባለቤት የሌለው ስራ፣ የፎቶግራፍ ስራን በተመለከተና የታተመ አንድ ቅጅ ለግል ፍጆታ ማዋልን የሚመለከቱ አዳዲስ ተካተቱ ነገሮች መኖራቸውን በአንቀፅ በአንቀፅ ዘርዝረው አብራርተዋል፡፡ የዕደ ጥበብ ሥራዎችን በሚመለከት የበርን ኮንቬንሽን ሥራዎች በሚለው ትርጉም ውስጥ ያካተተው በመሆኑ የኛም አዋጅ ይህንኑ መስመር ተከትሏል ብለዋል፡፡

የጋራ አስተዳደር ማህበር አመሰራረት፤መማላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፤ ስልጣንና ተግባር፤በጀት፤የሂሳብ መዛግብት፤ዕውቅና ስለመሰረዝና ሮያሊቲ የመክፈል ግዴታ በሚመለከት

በማሻሻያ አዋጁ በአንቀፅ 32 እና በተከታዮቹ እንዲካተት መደረጉን ገልፀዋል፡፡ባለቤት ከሌላቸው ስራዎች ስለሚሰበሰብ ሮያሊቲ በተመለከተም በአንቀፅ 39 የተመለከተ መሆኑን ገልፀው ቀደም ብሎ እጅግ አሳሳቢ የነበረው የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አዋጁን የማስፈፀም ሚና እንዲታከልበት የተደረገ መሆኑን ጠቅሰው መ/ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት መብትን የሚጥሱ ቅጂዎችን ሊይዝ ይችላል ብለዋል፡፡

የጋራ መብት አስተዳደር ባለመብቶች ማለትየቅጅና ተዛማጅ መብቶች ባለቤቶች መብቶቻቸውን በጋራ ለማስተዳደር በጋራ የሚያቋቁሙት ማህበር እንደሆነ በአዋጁ የትርጓሜ ክፍል የተቀመጠ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ሙሉ ወሰን ይሄ ሥርዓት ባለመብቶች በተናጥል ሊያገኙዋቸው የማይችሉዋቸውን ተጠቃሚዎች፣ ሊደርስባቸው የማይቻላቸውን ቦታዎች የሚያገናኝ ድልድይ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡የጋራ አስተዳደር ማህበራት ሚናን በተመለከተ ባለመብቶችን እና ተጠቃሚዎች ማገናኘት፤ የመብቶቹንመከበር መከታተል፤የባለመብቶችን የመደራደር አቅም ማሳደግ ወዘተ እንደሆኑ የገለጹት ጽሁፍ አቅራቢው የነዚህ ማህበራት መጠናከርና መጎልበት የስራ አመንጪዎች ትኩረታቸውን በአዳዲስ ፈጠራዎች ላይ እንዲያውሉ የማስቻል ሁኔታን እንደሚፈጥር ገልፀው ለሀገር ጂዲፒም የጎላ ጠቀሜታ እንዳለው አብራርተዋል፡፡

መንግስት ለዘርፉ እድገት ተገቢ የሆኑ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን እንዲያስቀምጥ እገዛ ማድረግና የቅጅ መብት ኢንዱስትሪው ለሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ማሳደግ ይችላሉ በማለት አክለዋል፡፡

የቅጅና ተዛማጅ መብቶች የጋራ አስተዳደር ማህበር አመሠራረትን በሚመለከት በአዋጁ ጥበቃ የሚያገኙ ስራዎች ባለመብቶች መብቶቻቸውን በጋራ ለማስተዳደር ማህበር ሊመሰርቱ እንደሚችሉ አዋጁ በአንቀፅ 32 ስር የሚያስቀምጥ መሆኑን ጠቅሰወው ጽ/ቤቱ ደግሞ እውቅና የሚቸራቸው መሆኑን የሚመሰረቱትም ትርፍ ላልሆነ ዓላማ (civic society) መሆኑን አደረጃጀቱም በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን መሆኑን በማብራራት የጋራ አስተዳደር ማህበራትን ለመመሥረት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች በአንቀጽ33 ስር ተመለከቱቱ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

የጋራ አስተዳደር ማህበሩምስረታ ዕውቅና በጽ/ቤቱ እንዲሰጠው ማመልከቻ በጽኑፍ የሚቀርብ ሆኖ የአባላት የፈጠራ ስራ ዓይነት መግለጫ፤የውስጥ የአሰራር ደንብ፣የመመስረቻ ጽሁፍ እንዲሁም በስሩ የተቋቋሙ የዘርፍ ማህበራት ዝርዝርና የአባላት ስም ተያይዞ ለጽ/ቤቱ መቅረብ ይኖርበታል

ያሉት አቶ ወሰን አንድ የጋራ አስተዳደር ማህበር በስሩ የሚያቀቁማቸው የዘርፍ ማህበራት ቁጥር ከ ሶስት ማነስ እንደሌለበት ጨምረው ገልፀዋል፡፡

የቅጂና ተዛማጅ መብቶች የጋራ አስተዳደር ሥልጣንና ኃላፊነትን በሚመለከት የአዋጁ አንቀፅ 34 ላይ የተቀመጡት መሆናቸውን ጠቅሰው በአዋጁ ጥበቃ ያገኙና የውጭ ሀገር ጥበቃ ያላቸውን ሥራዎች ከሚጠቀሙ ሰዎች ሮያሊቲ የመሰብሰብና መብት ላላቸው አባላት የማከፋፈል፤የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ ረቂቅ የሮያሊቲ ክፍያ ቀመር በማዘጋጀት ለጽ/ቤቱ ማቅረብና ሲፀድቅም ተግባራዊ ማድረግ፤ የሮያሊቲ አሰባሰብና አከፋፈልን አስመልክቶ ዝርዝር የአሰራር መመሪያ በማዘጋጀት ማቅረብና ሲፀድቅም ተግባራዊ ማድረግ፤ ስራዎችን ለህዝብ ለማቅረብ ከሌሎች አገራት ለሚገቡ የባንድ ወይም የክወና ቡድኖች እንዲሁም ለስነ ጥበብ ስራዎች አውደ-ርዕይ አቅራቢዎች በተመጣጣኝ ክፍያ ፍቃድ የመስጠት፤ባለቤት የሌላቸው ስራዎችን ሮያሊቲ በመሰብሰብ ለጽ/ቤቱ ገቢ የማድረግ፣እንደዚሁም ሌሌች ተግባራትን የሚያከናውኑ መሆናቸውን በዝርዝር አስረድተዋል፡፡ በአንድ ሙዚቃ ውስጥ ኮምፖዘር፣ ዜማና ግጥም፣ ፕሮዲዩሰር ወዘተ መኖራቸውን ጠቅሰው የበርን ኮንቬንሽንን ኢትዮጵያ ያልፈረመች በመሆኑ በመርህ ደረጃ የውጭ ሀገር ሥራዎች ጥበቃ አይሰጣቸውም በልዩ ሁኔታዎች ግን የውጭ ሥራዎች ጥበቃ የሚሰጥባቸው ሁኔታዎች የተቀመጡ መሆኑንና ቀደም ብለው ፅሁፋቸውን ያቀረቡት አቶ ታምራት የዘረዘሯቸው በመሆኑ እንደማይደግሚቸው ገልፀው የእንካ ለእንካ ስምምነት ከሌላ ሀገር ጋር ቢኖረን የዛ ሀገር ሥራ በእኛ ሀገር ጥቅም ላይ ሲውል ሮያልቲ ተሰብስቦ የሚላክ ሲሆን እነርሱም በተመሳሳይ መልኩ ይልካሉ ማለት ነው ብለዋል፡፡

ሮያሊቲ አንድ ጥበቃ የተደረገለት ስራ ከንግድ ስራ ጋር በተያያዘ ጥቅም ላይ ሲውል ተጠቃሚው ለባለመብቱ የሚከፍለው የአገልግሎት ክፍያ መሆኑን ገልፀው ጥበቃ ያገኘን ማንኛውንም ሥራ ለንግድ ዓላማ ጥቅም ላይ የሚያውል ማንኛውም ሰው የሮያሊቲ ክፍያውን ለሚመለከተው የጋራ አስተዳደር ማህበር የመክፈል ግዴታ እንዳለበት አውስተዋል፡፡

ሮያሊቲ ሊከፍሉ የሚገባቸውን አካላት ዝርዝር ወደፊት የጋራ አስተዳደር ማህበሩ ይፋ የሚያደርገው ጉዳይ እንደሆነ ጠቁመው የሌሎች ሃገራት ተሞክሮ እንደሚያሳየው ሮያሊቲ መክፈል የሚጠበቅባቸው አካላት ዋና ተጠቃሚዎች (Essential Users)-ሥራቸውን ከሙዚቃ ውጪ ማከናወን የማይችሉ (የምሽት ክበባት፣ ብሮድካስት ወዘተ)፤ እንደ አስፈላጊነቱ የሚጠቀሙ(Important Users)- ሙዚቃ ከፍተኛ ዕገዛ የሚያደርግላቸው (ሆቴሎች፣ ቡና ቤቶች

ወዘተ)፤በአንዳንድ ሁኔታዎች የሚጠቀሙ (Incidental Users)- ሙዚቃን እንደአጋጣሚ የሚጠቀሙ (ለምሳሌ ሎጆች፣የውበት ሳሎኖች፤ ወዘተ)

ባለቤት ከሌላቸው ስራዎች የሚሰበሰብ ሮያሊቲን በተመለከተ ባለቤት የሌለው ስለመሆኑ በፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠበት ስራ እንደሆነ አዋጁ በአንቀጽ 2(2)(34) ስር የስራው አመንጪ ወይም መብት የተላለፈለት ሰው በህይወት የሌለ ወይም የመጥፋት ውሳኔ የተላለፈበት ሲሆን እና መብቶቹን በባለቤትነት የሚያስተዳድር አካል የሌላቸው ስራዎች እንደሆኑ የተመለከተ መሆኑን ገልፀው ከእነዚህ ስራዎች የሚሰበሰብ ሮያሊቲ ለዘርፉ ልማት መዋል ያለበት በመሆኑ በጋራ አስተዳደር ማህበራት አማካኝነት ተሰብስቦ ለመንግስት ገቢ የሚደረግበት መንገድ በማሻሻያው (አንቀጽ 39(3)) እንዲካተት ተደርጓል ብለዋል። የካናዳ ኮፒራይት አክት orphan works ሚላቸው ሲሆን በእስራዔል እንዲሁም በሌሎች ሀገራት ይሄ ገንዘብ ለመንግሥት ገቢ የሚደረግ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የዳኝነት ስልጣንን በተመለከተ ከአዋጁ ጋር በተየያዘ የሚነሱ ከውል ውጭ ስለሚደርስ ሃላፊነትን የሚመለከቱ ጉዳዮች በስተቀር የፍትሐ ብሔር ክርክሮችን የመዳኘት ስልጣን የሚኖረው ጽ/ቤቱ የአእምሯዊ ንብረት ትሪቡናል ስለመሆኑ በአንቀጽ 44(1) ተቀምጧል ያሉት አቶ ወሰን ተሪቢውናሉ የሚመለከታቸው የፍትሓብሔር ክርክሮች በሮያሊቲ ተመን አወሳሰንና አከፋፈል ላይ የሚነሱ ክርክሮች፣ከመብት ማስተላለፍ ወይም ፍቃድ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ለሚቀርቡ አቤቱታዎች፣ለግዴታ ፍቃድ በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ ባለመብት ተመጣጣኝ ክፍያ እንዲያገኝ ውሳኔ የመስጠት፣የቅጅ መብት የሚያስገኙ ሥራዎች ማባዣና ማሰራጫዎች ላይ በሚጣል የሌቪ መጠን ለሚነሱ ክርክሮች ውሳኔ የመስጠት ስለመሆናቸው በዝርዝር ካብራሩ በኂላ ፅሁፋቸውን የደመደሙ ሲሆን አወያዩም ለቀረበው ፅሁፍ አቶ ወሰንን አመስግኖ ለሻይ እረፍት ተወጥቷል።

<u>አቶ ደረጄ ወርቁ - አወያይ (የሕግ አማካሪና ጠበቃ)</u>

ከሻይ እረፍት በኂላ አወያዩ አሁንም ተወራራሽነት እና ተያያዥነት የላው ሶስተኛ ፅሁፍ በወ/ሪት ሠብለ ገብረጊዮርጊስ የሚቀርብ መሆኑን በመግለፅ ፅሁፉ አቅራቢዋን በቀጥታ ወደ መድረኩ ገብዘዋቸዋል።

## ወ/ሪት ሠብለ ገብረጊዮርጊስ - (የሕግ አማካሪና ጠበቃ እንዲሁም በዘርፉ ልምድ ያላቸው ባለሙያ)

የሚቀርበው ፅሁፍ የኮፒራይት የጋራ አስተዳደር ማኅበራት አመሠራረት እና አሠራር በንጽጽር መሆኑን በመግለፅ የፅሁፉ ይዘት የጋራ አስተዳደር ማኅበራት መመስረት ስፈለገበት፣ አመሠራረትና አሰራሩ፣ የአንዳንድ አፍሪቃ አገራት ልምድና እይታ፣ የሀገራችን የቅጂ መብት የጋራ አስተዳደር እንዲሁም አንዳንድ ጥቆማዎች እንደሚኖረው በማስቀመጥ ወደ ገለጻው የገቡ ሲሆን ኮፒራይት መብቶች ዘርፈብዙ መሆናቸውን ጠቅሰው መብቶቹ የሚከፋፈሉ መሆኑንና የማባዛት መብትን በመያዝ ሌሎች መብቶችን ማስተላለፍ የሚቻል መሆኑን ጠቁመው የቅጂና ተዛማጅ መብቶችን ለማስተዳደር የጋራ አስተዳደር ማኅበር መኖሩ ጠቀሜታ እንዳለው አብራርተዋል፡፡

የቅጂ መብት የጋራ አስተዳደር ማለት የመብቱ ባለቤቶች በሥራቸው ላይ ያላቸውን መብቶች ለዚህ ዓላማ ለተቋቋመ ማህበር ወይም አካል በማስተላለፍ ሥራዎቻቸውን በጋራየሚያስተዳድሩበት ስርዓት እንደሆነ ጠቅሰው የመብቶቹ ባለቤቶች ይህን የማስተላለፍ ተግባር ለተቋሙ ፍቃድ በመስጠት ወይም ሙሉ በሙሉ በማስተላለፍ ሊተገብሩት እንደሚችሉ ገልፀው መብቶቹ የተላለፉለት የጋራ አስተዳደር ማህበር የባለመብቶቹን ጥቅም ለማስከብር ዓላማ ስራዎቹን ያስተዳድራል ብለዋል፡፡ Collective management ወይም የጋራ አስተዳደር የጀመረው በፈረንሳይ ሀገር እ.አ.አ ከ1777 ጀምሮ እንደሆነ ነገርግን አሁን አሁን ከቴክኖሎጂው ምጥቀት ጋር ተያይዞ የኮፒራይት መብቶች በቀላሉ እንዲጣሱ ምክንያት ሆኖዋል ብለዋል፡፡ ዋና ዓላማቸው የዓባላቱን ወይም የሥራ አመንጪዎችን መብት ማስጠበቅ፣ ስራው ጥቅም ላይ ሲውል የመቆጣጠር፣ ከተጠቃሚዎች ጋር በመደራደር፣ ፍቃድ የመስጠት፣ ሮያሊቲዎችን የመሰብሰብ፣ ለመብቶቹ ባለቤቶች እንደየድርሻቸው የማከፋፈል ሥራዎችን የሚሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

የጋራ አስተዳደሩ ያስፈለገበት ምክንያትን በተመለከተ በአንድ አገር የቅጂና ተዛማጅ መብቶች ሕግ ለስራ አመንጪዎች ወይም ለመብቶቹ ባለቤቶች የሚሰጡት መብቶች በባህሪያቸው በግለሰብ ደረጃ ለማስተዳደር አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ ሥራዎቹ ጥቅም ላይ ሲውሉ መቆጣጠርና መብቶቹ ማስከበር በተለይ በአሁኑ ጊዜ አስቸጋሪ እንደሆነ የጠቀሱት ፅሁፍ አቅራቢ ለዚህ አስቸጋሪነት እንደምክንትነት ያወሱት የመብቶቹና በአንድ ስራ ላይ መብት ያላቸው ሰዎች መብዛት፤መብቶች ጥቅም ላይ የሚውሉበት መንገድ መስፋት፤ ሥራዎች የሚሰራጩበት እንዲሁም የሚከወኑብት ዘዴዎች መብዛት፤ ሉላዊነትና የቴክኖሎጂ እድገቶች ወዘተ ጠቅሰዋል፡፡ እነዚህ ማህበራት ያስፈለጉበት አግባብ ከሁለት አንፃር ከፍሎ ማየት የሚቻል ሲሆን የመጀመሪያው ከሥራው

አመንጪ አንፃር ሲሆን ሌላው ደግሞ ከተጠቃሚው አንፃር እንደሆነ አብራርተዋል፡፡ የባለመብቱን ጥቅም ከማስከበር አንፃር ባለመብቱ በተናጠል ከሚሆን ይልቅ በጋራ የማስተዳደር ተቋማት አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከተጠቃሚዎች አንፃር ደግሞ በኮፒራይት የሚጠበቀው የኢኮኖሚና የሞራል መብቶች እንደመሆናቸው መጠን ለማህበረሰቡ የተሌዩ ሥራዎችን በመፍጠር በጎ አስተዋፅዖ ያበረክታሉ ብለዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር በአዋጁ አንቀፅ 9 እስከ 19 ገደማ ያሉት ድንጋጌዎች ጥበቃ የማይደረግላቸው በመሆናቸው ማህበረሰቡም በነዚህ የመጠቀም ሁኔታ መኖሩን አክለዋል፡፡ ሌላው ከተጠቃሚው በኩል ለው ፋይዳ በየሥራ አመንጪው ቤትና አድራሻ ከመሄድ ይልቅ ማህበሩ ጋር ሄዶ መደራደር የጎላ ጠቀሜታ አለው ሲሉ ተደምጠዋል፡፡

አንድ የመብት ባለቤት ስራውን በራሱ ላስተዳድር ቢል የሚያወጣው ወጪ እጅግ ከፍተኛ መሆኑ - ማን ለምን ተጠቀመ የሚለውን መለየት እንዲሁም ከሁሉም የስራው ተጠቃሚዎች ጋር በመደራደር ፍቃድ መስጠትንና ክፍያዎችን መሰብሰብ ባለመብቱ ላይ ከፍተኛ የወጪ ጫና የሚያሳድር በመሆኑ እነዚህ የአስተዳደር አካላት ይህን በቀላሉ ለማስተዳደር ይችላል ብለዋል፡፡

በአንድ ቦታ ላይ ተጠቃሚው የሚፈልጋቸውን ስራዎች በቀላሉ ያገኛል (ተደራሽነት)የተቀመጡ ታሪፎችን በመከተል እንደአጠቃቀሙ ይክፍላል፤ በፍቃዱ መሰረት ይጠቀማል፤ ጥበቃ የሚደረግለትን ስራ በሕጋዊ መንገድ መጠቀም ያስችላል ብለዋል፡፡

ሁሉም የጋራ አስተዳደር ተቋማት የሚከተሉት አንድ ሞዴል አለመኖሩን ጠቅሰው በሚያስተዳድሯቸው መብቶች አይነት (የሚንቀሳቀስባቸው ዘርፎች)፤ አባላት የሆኑንኑት ባለመብቶች አይነት፤ሥራዎቹ ጥቅም ላይ የሚውልበት መንገድ (በኢንተርኔት፥ በሲዲ)፤ በሚሰሩበት አገር ያለው የሕግ መዋቅር (ፍቃድ ማስፈለግ/አለማስፈለግ)፤እንደየድርጅቱ ባህሪ መብቶች የሚገኙባቸው መንገዶች ወዘተ ምክንያቶች የሚለያዩ ቢሆንም በአሰራር ረገድ ተመሳሳይ ሲሆኑ በአብዛኛው በባለመብቶች ፍቃድ ተነሳሽነት የሚገኝ እንደሆነም አብራርተዋል፡፡

የዘፈን ደራሲዎች፣አቀናባሪዎች፣ ግጥም ፀሃፊዎች እና አሳታሚዎች  በስራዎች ላይ ያላቸውን መብት ያስተዳድራሉ፤ ሥራዎች በይፋ ሲከወኑ ከተጠቃሚዎች ሮያሊቲ በመሰብሰብ ለባለመብቶች ያስተላልፋሉ፤ ሥራዎች በሬዲዮ፣በቴሌቪዥን፣ ለማስታወቂያ ስራ እንዲሁም በቀጥታ ለሕዝብ ሲቀርቡ ሮያሊቲ መከፈል አለበት ብለዋል፡፡ ሆቴሎች፣ሬስቶራንቶች፣ባሮች፣ ሙዚቃ የሚያጫውቱ ቦታዎች፣ ቲያትር ቤቶች፣ የክወና ቤቶች፣ የስፓርት ቦታዎች፣ ሸቀጣ ሸቀጥ መሸጫ ሱዎች፣

ሞሎች፣ኤርፖርቶች፣ ሆስፒታሎች እና ማንኛውም ሙዚቃ የሚያጫውት ቦታ በክፍያ ፍቃድ ማግኘት አለባቸው በማለት በዝርዝር አስረድተዋል፡፡

በአብዛኛው አጠቃላይ ፍቃድ (blanket license) ለተጠቃሚዎች የሚሰጥ መሆኑን በማውሳት ዋጋ በስራው ተጠቃሚ አይነት የሚወሰን መሆኑን፤ በሌላ አኳኋን በፕሮግራም ላይየተመሰረት ፍቃድም ሊሰጥ የሚችል መሆኑን እንዲሁም በሕግ የተፈቀደላቸውን መጠን (የተፈቀድ ሲሆን) ለአስተዳደር በመቁረጥ ቀሪውን ለባለመብቶቹ ያቀርባሉ በመጨረሻም ከተሰበሰበው ገንዘብ በሳምፕሊግ ቴክኒክ ተመጣጣኝ ክፍያ ለባለመብቶች ይከፍላሉ ብለዋል፡፡

የሚካኒካዊ መብቶች የጋራ አስተዳደር ማህበራት (Mechanical Rights CMOs) የሙዚቃ፣ የስነ ፅሁፍ እና የድራማ ስራዎችን መባዛት የሚያስተዳድሩ ማህበራት መሆናቸውን ገልፀውየሜካኒካል መብት ማለት አንድን ስራ ከባለቤቱ ውጪ ያለሰው እንዲያባዛው የመፍቀድ መብት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ መብት የሚገኝባቸው ሁለት መንገዶች ያሉ ሲሆን አንድም በፈቃደኝነት (voluntary) ሲሆን በአስገዳጅነት (non-voluntary) ደግሞ ሌላኛው ነው ብለዋል፡፡ በአለም አቀፍ ደረጃ ከሚንቀሳቀሱ ተቋማት መካከል በተለይ ክወናን በተመለከተ በፈረንሳይ መሠረት ያደረገ ድርጅት መኖሩን ጠቁመዋል፡፡

የአፍሪካ አገራት ልምድና እይታ ከዚህ እንደሚከተለው የሚቃኝ መሆኑን የጠቀሱት ፅሁፍ አቅራቢ ወ/ሪት ሰብለ የአፍሪካ ሀገራትን የመረጡበት አግባብ በሁለት ምክንያት መሆኑንና እነዚህ 3 አገራት ብዙ ፈተናዎች የገጠሟቸው በመሆኑ እና የአፍሪካ አገራት መሆናቸው ደግሞ ለኢትዮጵያ ተሞክሮ መቅሰም የተሻሉ እንደሆኑ በማሰብ አእንደሆነ ገልፀው የኬኒያ፣ የናይጀሪያና የደቡብ አፍሪካ ልምዶች እንደሚከተለው ተንትነዋል፡፡

በኬንያ ተፈፃሚነት ያላቸው ሕጎችKenya Copyright Act of 2001 (“Kenya Copyright Act”) እና CMOs Regulations of 2004 መሆናቸውን፤ የጋራ አስተዳደር ማኅበራቱ አመሠራረት ከኬንያ ኮፒራይት ቦርድ ፍቃድ በማግኘት ለሁሉም ወይም ለተለያዩ የባለመብቶች ጥቅም ሊቋቋም እንደሚችሉ፤ ዓላማቸው ሮያሊቲዎችን ሰብስቦ ማከፋፈል እንደሆነ፣ የሮያሊቲ መጠን በማህብራቱ ተዘጋጅቶ ሲፀድቅ ተፈፃሚ የሚሆን ስለመሆኑ፣በተግባር በሀገሪቱ ውስጥ ከአንድ በላይ ማህበራት የሚገኙ ስለመሆኑ ከተነተኑ በኂላ የመንግስት ቁጥጥርና ክትትል በሚመለከት ፍቃድ ከመስጠትና ከመከልከል በተጨማሪ የኬንያ ኮፒራይት ቦርድ የጋራ ማህበር አስተዳደር ተቋማት አመታዊ ሪፓርትና ኦዲት የተደረገ ሂሳብ በአመቱ ማቅረብ ለባቸው መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ካጋጠማቸው

ችግሮች መካከልየኮፒራይት ቦርዱፍቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ላይ ደካማ መሆን፤ በሕጋቸው ላይ የተቀመጡ መንገዶችና እርምጃዎች አነስተኛ መሆን፤ ሮያሊቲዎችን ለማይገባቸው ሰዎች መክፈል፤ አግባብነት የሌለው የሮያሊቲ መጠን መጫን ዋነኞቹ እንደሆኑ ጠቅሰዋል፡፡

በናይጄሪያ ያለውን ሁኔታ በሚመለከት ተፈፃሚነት ያላቸው ሕጎች Copyright Act 2004 and the CMOsRegulations 2007 መሆኑን፤ የማኅበራቱ አመሠራረት ከናይጄሪያ ኮፒራይት ኮሚሽን ፍቃድ በማግኘት ለሁሉም ወይም ለተለያዩ የባለመብቶች ጥቅም ሊቋቋም የሚችሉ መሆኑን፤ ዓላማቸቸውም ሮያሊቲዎችን በመሰብሰብ ማከፋፈል መሆኑን ጠቅሰው የገንዘብ አጠቃቀማቸውም 30 በመቶ ለአስተዳደር ሲሆን ቀሪ 70 በመቶ ለአባላቱ የሚደርስ መሆኑን፤ የሮያሊቲ መጠን በማህበራቱ የሚቀርብ መሆኑን፤ የሕግ ስርዓቱ ከአንድ ማኅበር በላይ መኖርን የሚፈቅድ መሆኑን በመጥቀስ መንግሥት ፍቃድ በመስጠት/በመከልከል/በመሰረዝ የሚቆጣጠራቸው መሆኑን እንዲሁምዓመታዊ አፈፃፀምና ኦዲት ሪፓርት የሚቀበል መሆኑን፤ በማህበሩ አደረጃጀት ላይ ለውጥ ሲኖሩ የማሳወቅ ግዴታ ያለባቸው መሆኑን አብራርተዋል፡፡ በናይጄሪያ ካጋጠሙ ችግሮች መካከል በዋናነት ከኮፒራይት ኮሚሽኑ ጋር የፍርድ ቤት ክርክሮች በተደጋጋሚ ነበሩ መሆኑንጠቅሰዋል፡፡

በደቡብ አፍሪካተፈፃሚነት ያለው ሕግ South African Copyright Act of 1978 እና Regulations 2006 መሆኑን፤ የማኅበራቱ አመሠራረት ከኮፒራይት ሬጅስትራር እውቅና በማግኘት እንደሆነ፤ ዓላማቸው ሮያሊቲዎችን መሰብሰብና ማከፋፈል ሆኖ ለአስተዳደር ወጪ20 በመቶ ሲሆን ለባለመብቶቹ የሚከፋፈለው 80 በመቶ እንደሆነ አብራርተዋል፡፡ከአንድ በላይ ማህበራት የሚፈቀድ መሆኑን የጠቆሙት ፅሁፍ አቅራቢ፤ ፍቃድ በመስጠትና በማንሳት፤ ዓመታዊና ኦዲት ሪፓርት በመቀበል መንግሥት ቁጥጥር የሚያደርግባቸው መሆኑን፤ የኮፒራይት ሬጅስትራሩ በማህበራቱ ጠቅላላ ጉባኤ ውስጥ ኢንዲገኝ ማስገደዱም የቁጥጥሩን አድማስ የሚሰፋ መሆኑን ጠቅሰው የማህበሩን አደረጃጀትና አሰራር የሚቀይሩ ነገሮች ሲኖር ለሬጅስትራሩ ማሳወቅ ግዴታ እንደሆነ በመግለፅ የሶስቱንም ሀገራት ልምድና ተሞክሮ አስቀምጠዋል፡፡

ቀጥሎም ወደ ኢትዮጵያ የጋራ አስተዳደር ማህበር በመምጣት ተፈፃሚነት ያለው ሕግ የቅጂና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 872/2007 መሆኑን፤ ማኅበሩ የቅጂና ተዛማጅ መብቶችንበጋራ ለማስተዳደር በባለመቶች የሚቋቋም መሆኑን፤ አመሰራረቱም ከእእምሯዊ ንብረት ፅ/ቤት ፍቃድ በማግኘት መሆኑን፤ አሠራሩም ሮያሊቲዎችን መሰብሰብና ማከፋፈል መሆኑን የአስተዳደር ወጭ 30 በመቶ ሆኖ ቀሪው ለባለመብቶች የሚከፋፈል መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ማሕበሩ ከውጭ የሙዚቃ ባንዶች ወደአገር ውስጥ ሲገቢ ፍቃድ መስጠት፣ ሮያሊት መጠን ማዘጋጀት፣

የሮያሊት አከፋፍል መመሪያ ማዘጋጀትና የገቢ ግብር ቀንሶ ለገቢዎች ማቅረብ መሆኑን አብራርተዋል፡፡ፍቃድ በመስጠት ወይም በመከልከል፤ ሮያሊቲ መጠን በማፅደቅ፣ዓመታዊ አዲት ሪፓርት በመጠየቅ፤ የአፈፃፀም ሪፓርት በፈለገው ጊዜ በመጠየቅ ወዘተ መንግሥት ቁጥጥር የሚያደርግባቸው መሆኑን ጠቁመው ከዚህ ውጪ ያሉትን ጉዳዮች በተመለከተ ቀደም ብለው ፅሁፎችን ሲያቀርቡ የነበሩ ባለሙያዎች ስለዳሰሱት የሚያልፉት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በአጠቃላይ የጋራ አስተዳደር ማኅበራት መቋቋማቸው ጠቃሚ መሆኑን፤ በእኛ ሀገር ጥበቃ የሚደረግላቸው ሥረዎች ውስን መሆናቸው ምክንያቱም የኛ ሀገር ሥራዎች ብቻ እንጂ የውጭ ሀገር ሥራዎች በመርህ ደረጃ ጥበቃ የማይደረግላቸው መሆኑን አስታውሰው በጥያቄ መልክ ሁለት ነጥቦችን ያነሱ ሲሆን፤ እነዚህም የመጀመሪያው ማኅበሮቹ በራሳቸው ከውጭ ማኅበራት ጋር የእንካ ለዕንካ ስምምነት ያለመንግሥት ወይም ከፅ/ቤቱ እውቅነቀ ው|ጭ ማድረግ የሚችሉ መሆን አለመሆኑን አንስተው ይሄ ጉዳይ በእያንዳንዱ ዜጋ ላይ የሚያመጣው ሸክም ወይም እዳ ስላለ እንደሆነ አውስተው፤ በመቀጠልም በሀገራችን አንድ ሞኖፖሊ የሆነ ማኅበር ወይንስ ሴክቶራል የሆኑ ከአንድ በላይ ማኅበራት ናቸው ሊቋቋሙ የሚገባው በማለት ጠይቀው ገለፃቸውን ደምድመዋል፡፡

## አቶ ደረጄ ወርቁ - አወያይ (የሕግ አማካሪና ጠበቃ)

ፅሁፍ አቅራቢዎችን በአጠቃላይ ካመሰገኑ በኂላ ወ/ሪት ሠብለ ያቀረቡት ፅሁፍ ገላጭና ምጥን መሆኑን፣ የአፍሪካ ሶስት አገራት ተሞክሮና ልምድ ያብራሩልን መሆኑንና በሀገራችንም ያለውን ክፍተት ለማሳየት ጥረት ያደረጉ መሆኑን ገልፀው ሁሉም ፅሁፍ አቅራቢዎች ወደ መድረክ እንዲመጡ በመጋበዝ መድረኩን ለጥያቄመና መልስ እንዲሁም ለአስተያየት ለቤቱ ክፍት እንደሆነ ገልጸው እራሳቸው በተወሰኑ ጥያቄዎች የጀመሩ ሲሆን የቀረቡት ሶስቱም ፅሁፎች ተወራራሽ መሆናቸውን ጠቅሰው ከቅጂና ተዛማጅ መብት ጥበቃ ጋር በተያያዝ ለምሳሌ ከአድማስ ባሻገር እና የቀማኛ ዳኛ እንዲሁም ሌሎች ሥራዎች ተቀራራቢ ሆነው እናገኛቸዋለን፤ የተከበሩ ሜትር አፈወርቅ ተክሌ ውቢቷ ኢትዮጵያን ስለዋል የርሳቸውን ቅርፅ በመያዝ ሌላ ሰው ቢስለው ምኑ ነው የሚጠበቀው የሚል ካነሱ በኂላ በቀጥታ መድረኩን ለተሳታፊው ክፍት አድርገዋል፡፡

## አቶ ታምራት ኪዳነማርያም - ፅሁፍ አቅራቢ፣ የማኅበሩ ፕሬዝዳንት እንዲሁም የሕግ አማካሪና ጠበቃ

አዌዩ ያነሱት ጥያቄ መሠረታዊ መሆኑን ለምሳሌ አንድ የእግር ኳስ ጨዋታ ላይ የሚዘግቡ ጋዜጠኞች አንድ ጎልን ሲገልፁ በተመሳሳይ መንገድ ይገልፃሉ፡፡ ፓተንት ላይ አዲስ (new)፣ የመጠቀ (novel)እና በመስኩ ያሉ ተመራማሪዎች የሚያመራምር መሆንን የሚጠይቅ ሲሆን በኮፒራይት ላይ ግን ይህ ዓይነት መስፈርት እንደሌለ ጠቁመዋል፡፡

## አቶ ምርምር ጥጋቡ - ከፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት

1. የሮያልቲ ክፍያን በተመለከተ የንግድ ሥራ መኖርን ይጠይቃል፡፡ የንግድ ሥራ ከትንሹ የንግድ ፈቃድ ባለቤት እስከ ላይ የተለጠጠ ነው፡፡ ስለዚህ ተጠቃሚውንና ባለቤቱን መሠረት ያደረገ ነው ወይ? ከኮፒራይት ጥበቃ ሕግ አንጻር ንግድ ማለት ምንድነው?
2. የደቡብ አፍሪካ ተሞክሮን በተመለከተ ክወናን (performance) አስመልክቶ ብቻ ሮያልቲ የተቀመጠ መሆኑ ከሀገራቸው ታሪክ ጋር የተቆራኘ ነውና የኛም ሀገር ሕግ ሲቃኝ ከታሪካችን አንፃር መሆን አለበት ብለዋል፡፡
3. ማህበራቱ ከአንድ በላይና ብዛት ያላቸው መሆን እንዳለባቸው ጠቁመው አስፈላጊነቱም ጠንካራ እና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡
4. ባለቤት የሌላቸው ሥራዎች ጥበቃ የተቸራቸው መሆኑ እጅግ በጣም ጥሩ እንደሆነና እንዲያውም ባለቤት የሌላቸው ሥራዎች ላይ ሮያልቲ ከፍ ማለት አለበት ብለዋል፡፡
5. የትሪቢውናሉን በተመለከተ ከውል ውጭ ኃላፊነት የፍ/ቤት ሥልጣን ሲሆን የተቀሩት ደግሞ በትሪቢውናሉ የሚታዩ ናቸው፡፡ ከትሪቢውናሉ የሥልጣን ክልል ውጭ ያሉ ጉዳዮች ለትሪቢውናሉ ቀርበው ሲታዩ ከቆዩ በኋላ መብቶችን የሚያጣብቡ ሁኔታዎች ቢፈጠሩ እንደ አሠሪና ሠራተኛ ሕግ ማጣጣሚያ የሚሆን ሕግ ወይም የሰበር ውሳኔ ስለመኖር አለመኖሩ ጠይቀዋል፡፡

## አቶ አሠፋ አሊ - የሕግ አማካሪና ጠበቃ

1. የፍ/ቤት ሥልጣንን በተመለከተ የተወሰኑ ችግሮች አሉ በማለት የጀመሩ ሲሆን እነዚህም፡-

1.1. የመጀመሪያው ችግር የአእምሯዊ ንብረት ጉዳይ የመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለመሆኑ በአዋጁ ላይ ተመልክቷል፡፡ ይሄ ደግሞ የይግባኝ መብትን በእጅጉ የሚያጣብብ ነው ብለዋል፡፡

1.2. ሕገ-መንግሥቱ ዳኝነት የፍ/ቤት ሥልጣን ነው በማለት በግልጽ መርህ የተቀመጠ ይሁን እንጂ ይሄ ሥልጣን በተለያየ አግባብ እየተሸራረፈ ለተለያዩ የአስተዳደር አካላት መሰጠቱ አግባብ አይደለም ብለዋል፡፡

1.3. ትሪቢውናሉ የሚያያቸው ጉዳዮች የመጨረሻ ናቸው ወይስ ይግባኝ ይባልበታል? ለየት የሚል ጉዳይ ለፍ/ቤት ሲቀርብ ይህን ሊያይ የሚችል ልዩ ልዩ ችሎቶች በየፍርድ ቤት የሚቋቋሙበት ሁኔታ ቢኖር በማለት ጠቁመዋል፡፡

2. የበርን ኮንቬንሽን አባል አይደለንም ካሉ በኋላ ለምን አባል አልሆንም? በማለት ጠይቀው መብቶችን ለማስከበር ክፍተቶች በአግባቡ መሙላት መቻል አለበት ብለዋል፡፡
3. እግድ በፍ/ቤት የሚሰጠው የክርክር ጥንካሬን አይቶ ነው በሚለው የማይስማሙ መሆኑን ጠቁመው ምክንያታቸውን ሲጠቅሱ እግድ የሚሰጠው ማስረጃ ሳይቀርብ የፍሬነገር ክርክር ሳይደረግ በመሆኑ የክርክር ጥንካሬን ለማየት አይቻልም ብለዋል፡፡
4. ለሞራል ተቃራኒ የሆነ ሥራ እንዴት በኮፒራይት ሕግ ጥበቃ ይደረግለታል? የሕግ የመጨረሻ ፍሬ አፈፃፀም ሆኖ ሳለ የማይፈፀም መብት ለምን ጥበቃ ወይም እውቅና ይሰጠዋል?
5. አንድ ሰው የአንድን ሙዚቀኛ ታሪክ ቢፅፍ ጥበቃ ይሰጠዋል?
6. ለፊልምና ለድምፅ የተሰጠው ጥበቃ ለምን ልዩነት ኖረው?

<u>ጌዲዮን ወ/ዮሐንስ - ከኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማሕበር</u>

በዛሬው ዕለት የቀረቡት ፅሁፎች ብዙ ናቸውና መርኃግብሮች ታጭቀው ባይቀርቡ እንዲሁም በተግባር የሚታዩ ኬዞች እየተነሱ ውይይት ቢደረግባቸው የሚል ሁለት አስተያየቶችን ከሰጡ በኋላ ጥያቄ ወደ ማቅረብ ያመሩ ሲሆን እንደሚከተለው አቅርበዋል፡፡

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በቀረበ አንድ የኮፒራይት ጉዳይ ላይ ፊልሙ በሚመረቅበት ቀን እግድ ተሰጠ፡፡ ከዚያም እግዱ ይነሳ እንዲሁም ይህን ጉዳይ ለማየት ፍ/ቤቱ ሥልጣን የለውም የሚል አቤቱታ ሲቀርብ፤ ፍ/ቤቱ ሥልጣን የለውም የሚለውን አቤቱታ አውጡና አቤቱታችሁን አስገቡ ተባለ ከዚያም በአቤቱታው ላይ መልስ እንዲሰጥበት ፍ/ቤቱ አዘዘ፡፡ በዚህ መሃል ሌላ እግድ ከከፍተኛ ፍርድ ቤት ወጣ ካሉ በኋላ የኮፒራይት ጥበቃ

የሚሰጣቸው ሥራዎች በተለይ ፊልሞች የሚመረቁበት ሰሞን የታገዱ እንደሆነ ኪሣራው ትልቅ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

2. የቅጂና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ በራሱ ኢ-ሕገመንግሥታዊ ድንጋጌዎች የሉትም ወይ? ለምሳሌ በአዋጁ አንቀፅ 6 የኮፒራይት ጥበቃ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ቅድመሁኔታዎች ወትነትና የመቀረፅ ግዴታንያስቀምጣል፡፡ ሕገ-መንግሥቱ በአንቀጽ 40 (2) መሠረት ለtangible እና intangible ንብረቶች ጥበቃ የሚሰጥ መሆኑን የሚደነግግ ሆኖ ሳለ በኮፒራይት አዋጁ ተጨባጭ ያልሆነን ንብረት መቀረፅ ቅድመሁኔታ ነው መባሉ አግባብ እንደማይመስላቸው ጠቁመዋል፡፡
3. ከእግድ ጋር በተገናኘተፈፃሚ የሚሆነው ሕግ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ አንቀፅ 154 ወይስ የኮፒራይት አዋጁ አንቀፅ 33 ነው?
4. ከoriginality ወይም ከወጥነት ጋር በተያያዘ ጥያቄ ያነሱ ሲሆን ሥራዎች በሁለት የሚከፈል ሲሆን የመጀመሪያ ሥራ እና የመጀመሪያ ሥራን መሠረት አድርጎ የሚሠራ ሥራ (derivative and non-derivative works) በሚል ለሁለት የሚከፈሉ ሲሆን original ማለት ምንድነው የሚለው መሠረታዊ መሆኑን ካነሳስ ኤንድ ፊስት የሚል ታዋቂ ኬዝ መኖሩን ጠቅሶ ይዘቱም የሥልክ ማውጫ (phone catalogue directory) ከማዘጋጀት ጋር የተያያዘ እንደሆነ ጠቅሰው ወጥ ማለት ምንድነው የሚለው ምን ማለት እንደሆነ ጠይቀዋል፡፡
5. በሕግ ሰውነት የተሰጣቸው አካላት የወንጀል ተጠያቂነትን (corporate criminal liability) በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 410/96 ያልተመለከተ ሆኖ ሳለ ዐ/ሕግ ክስ አቅርቦ ክስ ይሻሻል ቢልም ፍ/ቤቱ ይህ ባለመሆኑ ምክንያት መዝገቡን የዘጋው ሲሆን ዐ/ሕግ ይግባኝ ብሎ የይግባኝ ምክንያት ተብሎ ደግሞ የተጠቀሰው የሥር ፍ/ቤቱ በሥ/ሥርዓቱ 113 መሠረት ፍ/ቤቱ አሻሽሎ ተከላከል ሊል ይገባ ነበር የሚለውን ተጨባጭ ኬዝ አንስተዋል፡፡
6. የCopyright infringement ከውል ውጭ የሚመነጭ ኃላፊነትን የሚያስከትል ሲሆን ትሪቢውናሉ constitutional ነው ቢባል እንኳ IP office ያቋቋመው tribunal ምን ዓይነት ጉዳዮችን እንዲያይ ታልሞ ነው የተቋቋመው?
7. የኮፒራይት ጥሰት የይርጋ ጊዜ በፍትኃብሔር ሕጉ ላይ የተቀመጠው 10 ዓመት የሚለው ወይንስ ለውል ውጭ ኃላፊነት የተቀመጠው 2 ዓመት? የሚል ጥያቄ አንስተዋል፡፡

## አቶ ደረጄ ፀጉ - ከአእምሯዊ ንበረት ፅ/ቤት

1. Patent በidea ላይ monopolyን የሚፈጥር ሲሆን copyright ደግሞ expression of idea ነው። ፓተነት ላይ novelty ላይ radical change ካልመጣ ጥበቃ አይሰጥም። ኮፒራይት ላይ መመዘኛው ግልፅ አይደለም ብለዋል።
2. ትሪቢውናል ማቋቋም ከፍ/ቤት ሥልጣን መንጠቅ ነው። ፍ/ቤትም ሆነ ትሪቢውናሉ ውሳኔ የሚሰጡ አካላት ቢሆንም ትሪቢውናሉ ላይ የሚሰየሙት አንደኛው ሕግ የተማረ ዳኛ ሲሆን ሌሎቹ ግን በተለያየ ዘርፍ የሰለጠኑ expertise ናቸው በምሳሌነትም ኢንጂነር፣ ፋርማሲስት ወዘተ ናቸው ብለዋል።

## አቶ ታምራት ኪዳነማርያም - ፅሁፍ አቅራቢ፣ የማኅበሩ ፕሬዝዳንት
## እንዲሁም የሕግ አማካሪና ጠበቃ

ለተነሱት ጥያቄዎች እና አስተያየቶች ተሳታፊዎችን አመስግነው በአእምሯዊ ፅ/ቤት የተቋቋመው ተሪቢውናል ከውል ውጭ ኃላፊነት ውጭ ያሉ ጉዳዮችን የሚያይ መሆኑን ነገር ግን ከትሪቢውናሉ ፈቀደሥልጣን ውጭ ያሉ ጉዳዮች በስህተት ለትሪቢውናሉ ቀርበው እየታዩ ባሉበት ሁኔታ የይርጋ ጊዜያቸው ቢያልፍ ምን ማስተንፈሻ አለው የሚለውን በሚመለከት የተነሳው ጥያቄ መሠረታዊ መሆኑን ጠቅሰው የአሠሪና ሠራተኛ ሕጉ በሰበር ውሳኔ ታግዞ ይህ ዓይነት ሁኔታ ሲገጥም ማስተንፈሻ እንዲኖረው ተደርጓል ብለዋል። የዳኝነት ሥልጣን ከፍ/ቤት ውጭ ለአስተዳደር አካላት ሊሰጥ የሚችል መሆኑ ይታወቃል። ትሪቢዩናሉ ከውል ውጭ ሃላፊነት ውጭ ያሉ ጉዳዮችን የሚያይ ሲሆን ከኮፒ ራይት መብት ምዝገባ ጋራ ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች የሚያይ ይሆናል ማለት ነው ብለዋል።

የበርን ኮንቬንሽን አባል መሆን በውጭ ሃገር ባሉንሥራዎች በሮያሊቲ መልክ ጥቅም እንዲያስገኙልን የሚያደርግ ቢሆንም አባል በመሆን የምንሸከማቸው ግዴታዎችም መኖራቸው ሊዘነጋ አይገባም ያሉት አቶ ታምራት በአውሮፓና በአሜሪካ ምሁራን የተፃፉ መፅኃፍቶችን በውድ ዋጋ እንድንገዛ ግዴታ ይጥልብናል ብለዋል።

ከእግድ ጋር በተያያዘ በፍርድ ቤት የሚሰጥ የእግድ ውሳኔ የክርክር ጥንካሬን መሠረት በማድረግ የሚሰጥ ይሆናል የሚለው ብዙ ሰውን ቅር ያሰኝ ይሁን እንጂ በተለይ በኮመን ሎው ሀገራት ለዲ የሚባል ዳኛ የእግድ ክርክር meritwise መሆን እንዳለበት የሚያቀነቅን መሆኑን ጠቅሰው እግድ

ዝምተብሎ የሚሰጥ እንደሆነ በተለይ ኮፒራይት ላይ ትልቅ ኪሣራን ሊያደርስ የሚችል ነው ብለዋል፡፡ ለምሳሌ አንድ አዲስ ፊልም ሊመረቅ ሲል የፍ/ቤት እግድ ቢወጣበት እግዱ ከሶስት አመታት በኂላ ሲነሳ ፊልሙም ሆነ ማጀቢያ ሙዚቃዎቹ ጊዜ የሚያልፍባቸው በመሆኑ ተመልካች አይኖረውም ስለሆነም የኮፒራይት ሥራዎች የፍ/ቤት እግድ ከመደበኛው እግድ መለየት መቻል አለባቸው ይህ የሆነበት አግባብም በጥናት እንጂ እንዲሁ አለመሆኑን አብራርተዋል፡፡

ከሞራል ተቃራኒ የሆኑ ሥራዎች ለምን በኮፒራይት ሕጉ ጥበቃ ይደረግላቸዋል የሚለው ብዙ ጊዜ በሕግ ት/ቤትም ሆነ በሥራው ዓለም አከራካሪ እንደሆነ ገልፀው የጥበቃው ምክንያትን ያስረዱ ሲሆን የመጀመሪያው ሥራው ከሞራል ተፃራሪ ነው አይደለም የሚለውን በመወሰን ረገድ የሚደረገው የመመርመር ሥራ ወደ ሴንሰርሺፕ የሚያመራ ሲሆን ይሄ ደግሞ የማይቻል መሆኑን እና ሰዎች ሃሳባቸውን በነፃነት የመግለፅ መብትን የሚያጣብብ በመሆኑ እንደሆነ በመግለፅ ይህ ማለት ግን የሚመለከተውን የፕሬስ ሕግ የሚጠሱ ሥራዎች አያስጠይቁም ማለት እንዳልሆነ ሰፊ ገለፃ ሰጥተዋል፡፡ ከሞራል ተቃራኒ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ካሣ ይከፈል የሚለው የሚያስማማን ቢሆንም ሌሎች ሰዎች ያገኙትን ብልፅግና ይሰጠኝ የሚለው ግን አግባብ አይመስለኝም ብለዋል፡፡

ታሪኩ የተፃፈበት አንድ ሙዚቀኛ ወይም ሌላ ሰው በኮፒራይት ይጠይቃል የሚል እምነት እንደሌላቸው ገልፀው ነገር ግን ፎቶው ያለአግባብ ቢለጠፍበትግላዊነቴ (privacy) ተጥሰዋል በማለት በlaw of person's ሊጠየቅ ይችላል ብለዋል፡፡

የኮፒራይት አዋጅ ለሥራዎች ጥበቃ ለመስጠት ወጥነት (ኦሪጅናሊቲ) እና መቀረፅ የሚያስፈልግ መሆኑን የሚያስቀምጥ መሆኑን ቀደም ብሎ ያነሱት መሆኑን ጠቅሰው ሕገመንግሥቱ ደግሞ የአእምሯዊ ንብረቶች ተጨባጭ (tangible) ባይሆኑም ጥበቃ ይሰጣቸዋል በማለት ያስቀምጣል ብለዋል፡፡ ለአእምሯዊ ንብረት ጥበቃን የሚያደርግ የመንግሥት አካል ደግሞ ሕገመንግሥቱ ላይ ያለውን ጥቅል ሕግ ዝርዝር ሕግ እንዲወጣ በማድረግ የሚያስፈጽሙ በመሆናቸው ለዚህ ዓይነት ንብረቶች ጥበቃ ለመስጠት ቅድመሁኔታዎች እንዲወጡ ሆኖዋል ብለዋል፡፡

ከእግድ ጋር ተያይዞ ተፈፃሚነት ያለው የአዋጁ አንቀፅ 33 ወይንስ የፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ አንቀፅ 154 የሚለውን በተመለከተ የኮፒራይት ጉዳዮች በልዩ ሕግ የተሸፈኑ እና አዋጁም የቅርብ ጊዜ በመሆኑ ተፈፃሚ የሚሆነው ሕግ አንቀፅ 33 ላይ የተቀመጠው መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የoriginal standard ምንድነው የሚለው ጥያቄን በተመለከተ ከአእምሮ ማፍለቅና አለመኮረጅ እንደሆነ የገለፁት አቶ ታምራት ኮፒራይት ቋሊቲ ወይም ጥራትን መሠረት ያደረገ አለመሆኑን

ነገር ግን የአእምሮ ውጤት መሆን አለበት በማለት በአፅዕንዖት ገልፀዋል፡፡ በምሳሌነትም አንድ ዓለማቀፍ ተጨባጭ ኬዝ አንስተው ያብራሩ ሲሆን ዴቪድ የሚባል ሰው ያስቀመጠው ካሜራ በጉሬዛ ተነስቶ ፎቶ በጉሬዛው አማካኝነት ከተነሣ በኋላ ዊኪፒዲያ ይህን ፎቶ በድህረ ገፁ ላይ ለጠፈው ከዚያም ዴቪድ ዊኪፒዲያን የከሰሰ ይሁን እንጂ ፎቶው ያንተ የአእምሯዊ ውጤት አይደለም በሚል ውድቅ ሆኖበታል በማለት ይህን ፎቶ ሰውዬው ሳይሆን ተፈጥሮ እራሱ እንዳነሰው ነው የሚታሰበው ብለዋል፡፡

የኮፒራይት ጉደዮች በከውል ውጭ ኃላፊነት ሆነው የቀረቡ እንደሆነ የይርጋ ጊዜያቸው ከውል ውጭ ኃላፊነት ላይ የተቀመጠው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚነት የሚኖረው መሆኑን አውስተው የbusiness አሠራር በኮፒራይት ጥበቃ አይሰጠውም ምክንያቱም ሃሳብ ነው ያሉት ፅሁፍ አቅራቢ የbusiness process copyrightableባይሆንም አፃፃፉ ግን ጥበቃ የሚቸረው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

## አቶ ወሰን ሙሉ - በአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በኮፒራይት ዳይሬክቶሬት የቅጂ መብት ሕጋዊ ተፈፃሚነት ቡድን መሪ

የውጭ ሀገር ሥራዎች በband ሲቀርቡ የጋራ አስተዳደር ማሕበራት ፈቃድ ይሰጣሉ የሚል ሲሆን ሌሎች ሀገራትም የአንድ ከያኒ ሥራ በሚዲያ ሲሰራጭ ለከያኒ ክፍያ መክፈል ሲገባው ከያኒው እራሱ ክፍያ በመፈፀም እንዲታወቅ የሚያደርጉበት ሁኔታ መኖሩን ገልፀዋል፡፡ የአእምሯዊ ንብረት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች የሚቀርቡት ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሆነበት ምክንያት የሀገራት ተሞክሮ ታይቶ እና ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሸለ አደረጃጀት እና ውስብስብ ጉዳዮችን የማየት ልምድ አለው በሚል እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ የዳኝነት ሥልጣን ከፍ/ቤት እየተወሰደ ወደ ሌሎች አስተዳደር አካላት በሚወሰድበት ጊዜ የcheck and balance መርህ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚፈጥር ቢሆንም የተለያዩ ልዩ ወይም ስፔሻል ፍ/ቤቶች የሚመለከታቸውን ባለሙያዎች የሚያቅፉ በመሆኑ ተቀባይነት ያላቸው መሆኑ የሚታመን መሆን የገለፁት አቶ ሙሉ የኮፒራይት ጉዳይን ውስብስብ በመሆኑ እና የሌሎች ሀገራት ተሞክሮን በመቀመር ትሪቢዉናሉ እንዲቋቋም ምክንያት ሆኖዋል ብለዋል፡፡

የበርን ኮንቬንሽን አባል ለምን አልሆንም የሚለውን በተመለከተ በሂደት ላይ መሆናችንን ገልፀው ወደ መጨረሻው ቅርፅ እየሄደ መሆኑን ጠቁመው የኮፒራይት ጥበቃ ቅድመሁኔታዎች ወጥነትና መቀረፅ ከሕገመንግሥቱ ጋር የማይጣረሱ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

## ወ/ሪት ሡብለ ገብረጊዮርጊስ - (የሕግ አማካሪና ጠበቃ እንዲሁም በዘርፉ ልምድ ያላቸው ባለሙያ)

ሕገመንግሥተ ለአእምሯዊ ንብረቶች ተጨባጭ ባይሆኑ እንኳ ጥበቃ መደረግ እንዳለበት መደንገጉ የኮፒራይት አዋጁ fixation (መቀረፅ) ማስቀመጡ ጋር የማይጣረስ እንደሆነ መቅረፅ ማለት intangible ወደ tangible መቀየር ማለት እንዳልሆነ አስረድተዋል፡፡

በአንድ ሀገር ውስጥ አንድ የጋራ አስተዳደር ማኅበር ብቻ ያለው እንደሆነ ሞኖፖሊ የሚፈጠር በመሆኑ የማኅበራቱ ቁጥር ከአንድ መብለጥ እንዳለበት በአፅዕንዖት ገልፀዋል፡፡ በናይጄሪያና ሌሎች ሀገራት የኮፒራይት ጉዳይ በመደበኛ ፍ/ቤት ሳይሆን በልዩ ትሪቢውናል የሚታዩበት አግባብ መኖሩን የጠቀሱት ወ/ሪት ሡብለ ዓላማውም expediency and expertise ነው ብለዋል፡፡ የበርን ኮንቬንሽንን በአሁኑ ጊዜ መፈረም አለብን የሚል እምነት እንደሌላቸውም አክለዋል፡፡

## አቶ ደረጄ ወርቁ - አወያይ (የሕግ አማካሪና ጠበቃ)

ማሻሻያው ሲወጣ የኮፒራይት ጥበቃ የሚሰጠው የሥራ አመንጪው ከሞተ ለ50 ዓመት እንደሆነ በሕጉ የተመለከተ መሆኑንና ተፈፃሚ የሚሆነውም ከJanuary 1st መሆኑም ተደንግጓል ስለሆነም አንድ የሥራ አመንጪ ከሰኔ እስከ ጥር ባለው ጊዜ ውስጥ የሞተ እንደሆነ ይህንን ቫኪዩም ወይም ክፍተት በምን ይሞላል በማለት ጠይቀዋል፡፡

## አቶ ጌትነት ---- - ከቅጂና ተዛማጅ መብት ማኅበር

የእለቱ ውይይት እጅግ በጣም ጥሩ መሆኑን እንዲሁም የሕግ ባለሙያዎች ባሉበት መሆኑ ደግሞ የበለጠ መልካም መሆኑን ጠቅሰው ወደ ጥያቄና አተያየት የገቡ ሲሆን ይህም እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

1. አቀናባሪ በቅጂ መብትም ሆነ በተዛማጅ መብት ጥበቃ አልተደረገለትም ስለዚህ በዚህ ዙሪያ ብዙ አከራካሪ ነገሮች አሉ ብለዋል፡፡
2. የፍ/ሕጉ ስለ አጎራባች ወይም ተዛማጅ መብቶች የማያወራ መሆኑን፤ ተዛማጅ መብት ጥበቃ የተሰጠው በአዋጁ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከ1996 ዓ.ም. በፊት ያሉ ተዛማጅ መብት ባለቤቶች በምን አግባብ ነው የሚታዩት ብለዋል፡፡

3. Private management ይፈቀዳል ያልሸው የአዋጁን አንቀፅ 38 በግልፅ ይፃረራል ያሉት አቶ ጌትነት collective management societies ብቻ ናቸው ልቲ የመሰብሰብ ኃላፊነት ያለባቸው በማለት ልዩነታቸውን ገልፃዋል፡፡
4. በሀገራችን የሚገኝ Collective management organization (CMO) ከሌላ ሀገር CMO ጋር የሁለትዮሽ ስምምነት መግባት የለበትም በሚለው ጉዳይ የማይስማሙ መሆኑን ይልቁንም በየሀገራቱ ያሉት CMOs የእንካ ለእንካ ስምምነት መፈራረም መቻል ያለባቸው ስለመሆኑ ያላቸውን ልዩነት ገልፀዋል፡፡
5. የበርን ኮንቬንሽን ለታዳጊ ሀገራት exceptions አሉት በመሆኑም አባልሀገር መሆን ወይም መፈረም ለምን ስጋት ይሆናል?
6. እንደ የጋራ አስተዳደር ማኅበር አደራጅ multi CMO መኖራቸው ግጭቶችን ሊያበራክት እንደሚችል የጠቀሙት አቶ ጌትነት በምሳሌነት ያነሱትም ጉዳይ co-authors ቢኖሩና እነዚህ የጋራ ሥራ ባለቤቶች በተለያዩ ማኅበሩ ውስጥ አባላ የሆኑ እንደሆነ ከሰሩት ሥራ የሚገኝ ሮያልቲን የትኛው አካል ይሰበስባል ክፍፍሉም አስቸጋሪ ይሆናል በማለት አንድ የጋራ አስተዳደር ማኅበር በቂ የሚመስላቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

<u>አቶ ኃይላይ ታደሠ - የጋራ አስተዳደር ማኅበር አደራጅ ኮሚቴ አባልና</u>

<u>የኢ/ያ ኦውዲዮ-ቪዧል ሥራ አስኪያጅ</u>

በአዋጁ ላይ ውይይት ለማድረግ የሕግ ባለሙያዎች በመምጣታቸው የተሰማቸውን ደስታ ከገለፁ በኂላ ወደ ጥያቄያቸው የገቡ ሲሆን ጥያቄና አስተያየታቸው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. የመድረኩ ዓላማ ግልፅ ቢደረግ?
2. የቅጂ መብትና ተዛማጅ መብቶች ልዩነት አላቸው ወይንስ እኩል ናቸው? የቅጂ መብት ምንድነው? ተዛማጅ መብትስ?
3. በኢንደስትሪው ያሉ ሥራዎች ላይ በተግባር የሚነሱ ጥሰቶች አልታዩም፤ የሕጉ ቅኝት ብቻ ነው የተደረገው ብለዋል፡፡
4. በበርን ኮንቬንሽን ላይ ለታዳጊ ሀገራት ጠቃሚና ደጋፊ ድንጋጌዎች አሉት ብለዋል፡፡
5. የሙዚቃ ክሊፕ ሳውንድ ነው ወይስ ኦውዲዮ-ቪዧል ነው?
6. የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር የአእምሯዊ ንብረት ኮሚቴ ከእኛ ጋር በጋራ ቢሰራ የሚል አስተያ ሰጥተዋል፡፡

7. ከአፍሪካ ሀገራት ተሞክሮ ለመቅሰም ከተመረጡ ሀገራት መካከል ኬኒያ አንዷ ስትሆን በሀገሪቱ ውስጥ በሙስና ምክንያት በተለይም ፈቃድ (license) በማግኘት ረገድ ከፍተኛ ችግር የነበረ መሆኑን አንስተዋል፡፡
8. የጋራ አስተዳደር ማኅበር ሲቋቋም በቁጥር አንድ ሆኖ በዚሁ ስር ብዙ የዘርፍ አደረጃጀት (sectoral sructure) ቢኖር የተሻለ እንደሚመስላቸው ጠቁመዋል፡፡

<u>አቶ አዱኛ ጀቤሣ - ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት</u>

በኮፒራይት ወጥነት ለማረጋገጥ የምንጠቀምበት Substantial similarity test ማለት መለኪያው ምንድነው?

<u>አቶ ተመስገን ገ/ሥላሴ - የሕግ አማካሪና ጠበቃ</u>

የጋራ አስተዳደር መኅበር ግዙፍ የሆነ ስራ እንደሚሰራ ይገመታል፡፡ አዋጁ በግልፅ ማስቀመጥ የሚገባውን ነገር ሳያካትት አልፏል ብለዋል፡፡ ማኅበሩ ሲመሰረት ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ምዝገባ ጋር ያለው ንፅፅር እና ግንኙነት ምንድነው ግልፅ አይደለም ተጨማሪ የማሕበር ዓይነት ነው እየተፈጠረ ያለው? የጋራ አስተዳደር ማኅበሩ ትልቅ ኢንደስትሪ የሚመራ አካል መሆኑ ታውቆ በዚህ ረገድ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ የሚገባ መሆኑን እና ይህ የማይደረግ ከሆነ የከፋ ውጤት ሊኖረው ይችላል በማለት አሳስበዋል፡፡

<u>አቶ ደረጄ ወርቁ - አወያይ (የሕግ አማካሪና ጠበቃ)</u>

የተነሱ ሃሳብ፣ አስተያየቶች እንዲሁም ጥያቄዎች እጅግ በጣም ጥሩ መሆናቸውን ገልፀው ምላሽ የሚፈልጉ ጥያቄዎች የተነሱ በመሆናቸው ፅሁፍ አቅራቢዎቹ አስተያየታቸው የሚሰጡበት ሆኖ የዚህ መድረክ ዋና ዓላማ ግንዛቤ ማስጨበጫ እና የእውቀትና ተሞክሮ ልውወጥ ማድረጊያ የተለመደ የማኅበሩ መርሃግብር መሆኑን ጠቁመው በጥያቄዎቹ ላይ አስተያየት እንዲሰጥ መድረኩን ለፅሁፉ አቅራቢዎች ክፍት አድርገዋል፡፡

<u>አቶ ታምራት ኪዳነማርያም - ፅሁፍ አቅራቢ፣</u>
<u>የማኅበሩ ፐሬዝዳንት እንዲሁም የሕግ አማካሪና ጠበቃ</u>

ግንቦት 18 ቀን 2008 ዓ.ም. ባደረግነው ውይይት የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ቢሳተፉ የሚል ሃሳብ ስለነበረና የአእምሯዊ ንብረት ሕግ ደግሞ ከሌሎች ሕጎች አንፃር ሲገመገም ሕጉ በሚፈለገው ልክ

በማህበረሰቡም ሆነ በባለሙያ ዘንድ አልሰረፀም ያሉት አቶ ታምራት የዚህ ውይይት ዋና ዓላማ ቀደም ሲል በተጠቀሰው ቀን የተደረገው ትምህርታዊ ውይይት የቀጠለ መሆኑና በዋናት ግንዛቤ ለማስጨበጥ የተዘጋጀ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በኮፒራይት ሕጉ ላይ ጥበቃ ያልተሰጣቸው ወይም ስማቸው ያልተገለጸ አቀናባሪ ብቻ ሳይሆን ኤዲተር እና ሌሎች የሥራ ተሳታፊ ባለሙዎችም የሚገኙ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ማለትም ከ1996 ዓ.ም. በፊት ያሉ ሥራዎችን በተመለከተ የፍትሃብሔር ሕጉ ቀላል በማይባል ደረጃ ሽፋን የሚሰጥ መሆኑ ግልፅ ቢሆንም ለክወና ግን ሽፋን አይሰጥም ብለዋል፡፡

ዲጄ በምስል የተቀናበረን ሥራ እንደፈለገ ማጫወት አይችልም ነገር ግን የድምፅ ሪከርዲንጎችን እንደፈለገ ማጫወት የሚችል መሆኑን ይሄ ደግሞ መከወን መሆኑን ገልፀው የድምፅ ሪከርዲንግ ባለቤት የክወና ሥራን በተመለከተ የመከለከል ሥልጣን የለውም ብለዋል፡፡ Substantial similarity አለ ወይም የለም የሚለውን በተመለከተ ለፍ/ቤት ውሳኔ የተተወ ሲሆን በብዛትና በጥራት ረገድ ሊገመገም የሚችል መሆኑን ገልፀው ብዙውን እና ዋናው ክፍል የተወሰደ እንደሆነ ወይም ደግሞ ገበያን መሠረት ያደረገ መለኪያ ማለትም አንዱን ከገዛን ሌላውን መግዛት የማያስፈልግ ሆኖ በዚሁ ምክንያት ገበያ ያሳጣው እንደሆነ በማለት አብራርተዋል፡፡

<u>ወ/ሪት ሠብለ ገብረጊዮርጊስ - (የሕግ አማካሪና ጠበቃ እንዲሁም</u>

<u>በዘርፉ ልምድ ያላቸው ባለሙያ)</u>

Non-voluntary CMO በተግባር የተቋቋመ ያለ እንደማይመስላቸው ገልፀዋል፡፡ በተለያየ ሀገር ያሉ የጋራ አስተዳደር ማኅበራት ከኛ ሀገር ማኅበር ሚደርጉት ስምምነት reciprocal obligation ይዘው የሚመጡ በመሆናቸው አሁን ባለንበት ሁኔታ ተጨማሪ burden የሚያመጡብን በመሆኑ የሕዝብን ጥቅምና የባለመብቱን ጥቅም ማዕከል ማድረጉ ተገቢ ነው የሚል እምነት አለኝ ብለዋል፡፡ WIPO የሚለው በአንድ በኩል ያለውን ብቻ መሆኑን ጠቅሰው balanced መሆን አለበት ብለዋል፡፡ የCMO multiple መሆን monopolyን የሚያስቀር መሆኑ ግልፅ እንደሆነ የሥራ አመንጪዎች የመደራጀት መብትን መገደብ አስፈላጊ ባለመሆኑ protectionist መሆን እንደሌለብን ጠቁመዋል፡፡

## <u>አቶ ወሰን ሙሉ - በአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በኮፒራይት ዳይሬክቶሬት የቅጂ መብት ሕጋዊ ተፈፃሚነት ቡድን መሪ</u>

የስነ-ፅሁፍ ሥራ አመንጪ የሆነ ሰው ከሞተ በኋላ የጥበቃ ጊዜ ከJanuary 1st ጀምሮ የሚል መሆኑ ቀደም ብሎ ቢሞት ይህ ቫኪውም በምን ይሞላል የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ እንደሆነ ገልፀው ከውጭ ሀገር የተወሰደ ተሞክሮ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ CMO ቀደም ብሎ በcharities and societies ተመዝግቦ የነበረ ቢሆንም royalty ለመሰብሰብ የሚያስችለው ባለመሆኑ ከIP office ደግሞ እውቅና ሊሰጠው የሚገባ ስለመሆኑ ገልፀዋል፡፡

## <u>አቶ ደረጄ ወርቁ - አወያይ (የሕግ አማካሪና ጠበቃ)</u>

አወያዩ የቀረቡ ፅሁፎችን፣ የተነሱ ሃሳብ አስያየቶችን እንዲሁም ጥያቄዎችን ለወደፊት የሚያድጉ የሚበለፅጉ ሃሳቦች የተዘሩ እንጂ ያለቁ አለመሆናቸውን ጠቅሰው ያልተነኩ ሃሳቦች መኖራቸውን አስታውሰው ይበልጥ ፅሁፎች እንዲጎለብቱ የሚጠቅሙ መሆናቸው ከገለፁ በኋላ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ፅ/ቤት በፕሮግራሙ ላይ ላበረከቱት መልካም አስተዋፅዎ አመስግነዋል፡፡ በመቀጠልም ሶስቱም ፅሁፉ አቅራቢዎች መመስገን እንዳለባቸው ተሳታፊዎችም እጅግ የነቃ ውይይት እንዲሁም ጠቃሚ ሃሳቦችን ያነሱ መሆኑን ጠቅሰው ለሁሉም አካላት ምስጋና አቅርበው ውይይቱ ከቀኑ 9:30 ላይ ተጠናቋል፡፡

////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////